## መ. ወንጌልን ለሙስሊሞች የማድረስ መመሪያዎች

የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሙሉ ይዘት በሚገባ ስናጠናቸውና በሥራ ላይ ስናውላቸው፥ ለማንኛውም የወንጌል ሥራ፥ ለትምህርት፥ ለምክር እና ለእግዚአብሔር አገልግሎት ፍጹም መሠረት ይሆናሉ።

«ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስን በልባችሁ ቀድሱት። በናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን» (1 ጴጥ 3፡15)።

«ነገር ግን ሞግዚት የራስዋን ልጆች እንደምትንከባከብ በመካከላችሁ የዋሆች ሆንን፤ እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ፥ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና። ... በእናንተ በምታምኑ ዘንድ በእንዴት ያለቅድስናና ጽድቅ ነቀፋም በሌለበት ኑሮ እንደሄድን እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች ናችሁ፤ ... እየመከርንና እያጸናን እየመሰከርንላችሁም አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደሆንን ታውቃላችሁና» (1 ተሰ 2፡7-12)።

### ወንጌልን ለሙስሊሞች ማዳረስ

በተለመደው መልኩ ‹መስበክ› ብዙም ትርጉም የማይሰጥ መሆኑን ማወቅ አለብን። ሙስሊሞች ወደ ክርስቲያኖች ስብሰባ አለመሄድን እንደ አጠቃላይ ሕግ አድርገው ይወስዱታል። ይህ ደግሞ በግልና በዜና ማሠራጫዎች መጠቀምን ብቸኛ አማራጭ ያደርገዋል። በግል ሰው ለሰው ስንመሰክር ግን በመጀመሪያ ልዩ ተሠጥኦ በሁለተኛ ደረጃም በቂ ሥልጠና ያስፈልገናል።

መስካሪ ሊገነዘባቸው የሚያስፈልጉ ነገሮች፡-

* መጽሐፍ ቅዱስን በተለይም ወንጌልን መረዳት
* እስልምናን ባጠቃላይና በአካባቢው ያለውን ሁኔታ ማወቅ
* ሙስሊሙ ራሱንና በአካባቢው ያለውን ዓለም እንዴት እንደሚያይና ምን እንደሚሰማው መገንዘብ።
* በውጪ ያሉት ሊገባቸው የሚችል የግንኙነት ዘዴ መጠቀም



* ወንጌልን እንዳይረዱ የሚያግዳቸውን ባህላዊ ጉዳዮች ማስወገድ ያስፈልገዋል፥ ይህ ደግሞ የውንጌል ሥራ መሠረታዊ ነገር ነው።

እስልምና በሁሉም ቦታ አንድ ዓይነት አይደለም። እኛ ብቻ በራሳችን ማኅበረሰብ ውስጥ በባሕርይ፥ በትምህርት፥ በአመለካከት፥ በባህላዊ ጉዳዮች፥ በመሠረተ የእምነት አቋም፥ ወዘተ የተለያየን እንደሆንን አድርገን መውሰድ የለብንም፤ ሙስሊሞችም እንዲሁ የተለያዩ ናቸው። የሃይማኖቱ ሥርዓቶችና ቅርጾች ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም፥ ስለ ሃይማኖቱ ያላቸው እውቀትና ግንዛቤ፥ ወይም ከተለያየ ባህል የመጡ የተለያዩ ሰዎች ያላቸው አመለካከት፥ እውቀትና ግንዛቤ፥ ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም።

በእስልምና ውስጥ ካሉት ክፍሎች ጐን ለጐን ከፍተኛ የሆነ የፅንሰ-ሐሳብ ልዩነት አለ፤ ጥቂቶቹን እነሆ፡-

* አጥባቂ ሙስሊሞችና ዘመናውያን ለዘብተኞች አሉ።
* በቁርዓን ላይ ብቻ የተመሠረቱና በአንጻሩም ሐዲስን፥ ወይም ሁለቱንም እንደ ዋና የሚወስዱ አሉ።
* ጭፍን የሆኑ ወግ አጥባቂዎች እና በግሩም ሁኔታ የተመጠነ አቋም ያላቸው፤ (የሀኒፍን፥ የኢብንማሊክን፥ የአሽ-ሻፊን ወይም የሐንባሊን የሕግ ሥርዓቶች የሚከተሉ) አሉ።
* በጣም መንፈሳዊና ምስጢራዊ የሆነውን ‹ሙርሺድ› ወይም የ ‹ፒር› (ከመለኮታዊ ምንጭ የሆነ የነፍስ መመሪያ) ትምህርቶችን የሚከተሉ፥ የተለዩ ‹ቅዱሳንን› የሚያመልኩ፥ እንዲሁም ሁለቱንም የሚቃወሙ አሉ።
* ‹ሕግጋትን› የሚከተሉ ሙስሊሞችና እስልምናን በጣም መንፈሳዊ ለማድረግ የሚጥሩ አሉ።

ሙስሊሞች አንድ ዓይነት አይደሉም። በተጨማሪም ሙስሊሞች፡-

* የተማሩና ተራዎች
* ገጠሬዎችና ከተሜዎች
* የተለያየ ባህል፥ ልምድ፥ ባሕሪይ፥ ፍላጎት፥ ምኞት፥ አመለካከት፥ ኅብረተ ሰብ፥ ጎሳ ወዘተ ያላቸው ናቸው።

የተለያዩ ሰዎችን በአንድ መንገድና በአንድ ዓይነት ዘዴ መቅረብና መድረስ እንደሚቻል አድርጎ መውሰድ እውነትነት የሌለው ግምት ነው።

የተለያዩ ሰዎችን በአንድ መንገድና በአንድ ዓይነት ዘዴ መቅረብና መድረስ እንደሚቻል አድርጎ መውሰድ እውነትነት የሌለው ግምት ነው።

ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ያሉ ጽሑፎች ደረጃ በደረጃ ምን መደረግ እንዳለበት የሚናገሩ ዝርዝር ሁኔታዎች ሳይሆኑ፥ በሁሉም ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች የተሻለውን መንገድ እንዴት መምረጥ እንደምንችል የሚያሳዩ አጠቃላይ መመሪያዎች ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነገር፥ ሙስሊሞችን በወንጌል የመድረስ ጉዳይ (እንደሌላው ሁሉ) በክፍል ውስጥ ወይም ከመጽሐፍ ብቻ የምንማረው ነገር አይደለም። እውቀት ልምድንም ሆነ ባሕርይን ሊተካ አይችልም።

መመሪያዎቹን እንዴ ካወቅን፥ ባሉት ሰዎች ማንነት፥ በሁኔታዎቹ እና ባሉበት የአስተሳሰብ አድማስ መሠረት በተግባር ልንተረጉማቸው እንችላለን። የምንማረው አንድ ዓይነት የአቀራረብ ዘዴ በመጠቀም ወይም የምንናገረውን በአስተዋፅኦ በመንደፍ ወይም የትኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደምንጠቀም በማሰብ ሁሉንም በአንድ ዓይነት ለመሥራት አይደለም። በተቃራኒው ስጦታዎቻችንን ሁሉ ለማምጣት፥ በመረጃዎችና በእውቀት በልጽገን ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆነውን ታላቁን ያልተፈጸመ ሥራ፥ ለጠፉት ኃጢአተኞች በተለይም በባህል በኩል ያልታደሉትን ሙስሊሞች ማዳንን ለመፈጸም እስቲ በትንሹ ክርስቲያናዊ ነፃነትን እየተለማመድን እግዚአብሔር ያደረገንን እንሁን።

## የወንጌል ስርጭትን መገንዘብ

### የወንጌል ስርጭት

የወንጌል ስርጭት የሚለው ኃሳብ «ኢቫንጀሊዮ» ከተባለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም መልካም ዜናን ማምጣት ነው። እንዲሁም ‹መስበክ› ተብሎም ሊተረጎም ይችላል።

### ወንጌል

በእርግጥ መልካሙ ዜና እግዚአብሔር በቅድስናውና በጽድቁ የኃጢአታችን ዋጋ ከሆነው ማለትም ከሲኦል ነፃ ሊያወጣን ማቀዱ ነው። እግዚአብሔር ይቅር ሊለን፥ ሊያድነን፥ ደኅንታችን (ኢየሱስ ለ ደኅንነት) ሊሆን ፈቃደኛ ነው። እርሱ በክርስቶስ ሆኖ ወደዚህ ዓለም መጣ። ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ የሰው መልክና ባሕሪይ ይዞ ሥጋ ለብሶ ቢመጣም (ፊሊ. 2፡6-8)፥ ኃጢአትን አላደረገም። ነገር ግን በእኛ ፋንታ ለኃጢአታችን በመስቀል ለመሞትና ለመሰቃየት ራሱን አቀረበ። ይህንን ይቅርታ



ኢየሱስን እንደ አዳኛችን በማወቅ በግላችን ብንቀበል ተዋጅተናል። ማለትም ወደ እግዚአብሔር እንደገና በመመለስ፥ እንደ ገዛ ልጆቹ የርሱ ሆነናል ማለት ነው። እኛ ምንም ሳንሠራ በዚህ ችሮታ ብቻ አሁን በሰማይ፥ እግዚአብሔር ባለበት የዘላለም ደስታን እንካፈላለን።

እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ፍጹማን ለመሆን ባይችሉም እንኳ፥ ኃጢአትን ደጋግሞ ከመሥራት ለመራቅ ሁልጊዜ ጥረት ያደርጋሉ። ይህም የሚደረገው ደኅንነትን ለማግኘት ሳይሆን፥ ለባለ ውለታቸው ካላቸው ፍቅር የተነሣ ነው። በነርሱ ውስጥ የሚኖረው የእግዚአብሔር መንፈስ እየመራቸው እግዚአብሔርን እንዲከተሉት ኃይል ይሰጣቸዋል፤ እንዲሁም መንፈሳዊ እውነቶችን እንዲረዱ እያደረገ ኃጢአትን ሲሠሩ የማያቋርጥ መንጻት እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

ይህ ወንጌል በእውነት ለሰሚው ትርጉም ያለው የሚሆነው፡- እሱ ወይም እሷ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ባሕሪይ በፍጹም ቅድስናውና ጽድቁ መሠረት ሲረዱት፥ በቃሉ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን መመዘኛ ሲገነዘቡ፥ በኃጢአት የተሞላውንና የወደቀውን የሰውን ተፈጥሮ እንዲሁም ራሱን ማዳን ዓለመቻሉንና የኃጢአትን ባሕሪይ ሲያውቁ ብቻ ነው። የዚያን ጊዜ ብቻ ነው የደኅንነት፥ የኃጢአት ስርየትና ከእግዚአብሔር ጋር የመታረቅ ጉዳይ አስፈላጊ መሆኑን የሚታወቁ።

### የወንጌል ሥራ መመሪያዎች

ከሁሉ በፊትና በላይ ወንጌል ማሠራጨት ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰው፥ ስለ እግዚአብሔር ሕግ፥ ስለ ኃጢአትና መፍትሔው፥ ማለትም በክርስቶስ ሞትና በደሙ መፍሰስ ስለሚገኘው ስርየት የምሥራቹን ማስተላለፍ ነው። ሰዎች ምናልባት በምንናገረው ነገር ከፍተኛ ፍርሃት ሊሰማቸው ይችላል። ቁም ነገሩ ሰዎችን በማስፈራራት ለማሳመን ሳይሆን በግልጽ እንዲታያቸው መሆን አለበት።

ከዚህ ባሻገር እኛ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ያለን የተለያየ አመለካከት ምናልባት መንፈሳዊ የሆነውን ውይይት ሊያግድብን ይችል ይሆናል። ‹የኔ አባት ከአንተ አባት ይበልጣል› በሚለው የአቀራረብ መንገድ መጠቀም ምንም ዋጋ የለውም። ከ «ክርስትና» ጀብደኝነት እንጠንቀቅ!

ለአንድም ሙስሊም አላህ በከፍታዎች ላይ ከፍ ብሎ ያለ አምላክ ነው። አላህም በጣም ሩቅ ነው፤ ፍጹምና ሉዓላዊም ነው፤ ሊመለክ የሚችለውም በባሪያና ጌታ ግንኙነት መንገድ ዓይነት ነው። እሱ የተፈራ ነው!

መረዳት ያለብን አንድ ነገር አለ፡- አንድን ሙስሊም ደረጃ በደረጃ ልቡ እየተነካ ወደኛ ሐሳብ እንዲመጣ ለማድረግ ስለ እግዚአብሔር የሚከተሉትን ነገሮች ማስረዳት አለብን። እግዚአብሔር ስብዕና ያለው አምላክ ነው። እሱ ይጠነቀቅልናል፤

ይሰማናል፡ እንደ ልጆቹ ሆነን ልንቀርበው እንችላለን። ለእኛ የሚያስበው መልካም ሐሳብ ነው። እኛ በፈቃዳችን ልናከብረው እንጂ ክፉ ሊያደርስብን እንደሚያስብ ሁሉ ልንፈራው አይገባንም። እኛ ሁላችን ሙሉ በሙሉ በእርሱ ስለተደገፍን፥ ሌሎች ወኪሎች አያስፈልጉንም። እርሱም በራሱ ጉዳይ የተሞላና ለእኛ ምንም ጊዜ የሌለው አምላክ አይደለም። ከተሳሳትን በኋላ ይቅር እንዲለን ወደ እርሱ ስንቀርብ አይበቀለንም። የእርሱ የወደፊት ሐሳብ የታወቀ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ በቃሉ የታመነና ከተናገረውም አንዲት ፊደል እንኳ የማይቀንስ በመሆኑ ነው። እኛ ከርሱ ጋር የት እንደሆንን ልናውቅ እንችላለን፤ ምክንያቱም ከኃጢአታችን ተጸጽተን በንስሐ ወደ እርሱ ብንመለስ ይቅር እንደሚለን በቃሉ ተናግሮአልና። ቃሉ የማይሻርና መለኮታዊ ነው።

እንግዲህ ይህ እያንዳንዱን ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፊት ያለውን አቋም እንዲመለከት ያደርገዋል። ‹እኛ ድነናል› ብለን መናገር እንችላለን። ከታላቅ ምስጋና ጋር ይቅር መባላችንን፥ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የቀድሞው መለያየት መታደሱን መቀበል እንችላለን። በምንሞትበት ጊዜ የት እንደምንሄድ እናውቃለን።

ለሙስሊሞች፥ እነዚህ ጭፍን የድፍረት ንግግሮች ናቸው፤ ምክንያቱም የአላህ ፈቃድ አስቀድሞ አይታወቅም። እርሱ እንደፈለገ ነው የሚያደርገው። ምንም ነገር ሊያስገድደው ወይም ሊወስነው አይችልም። የተናገረውን ቃል መሻር ይችላል ይህንንም ደግሞ በተግባር አድርጓል!

### ወንጌልን ማሠራጨት መልካሙን የምሥራች ማካፈል ነው።

### ወንጌሉ ስለ ደኅንነት ይገልፃል።

ደኅንነት የእግዚአብሔር ድርጊት ነው። ለሰው ልጆች የተሰጠ ነፃ ስጦታ ነው። ደኅንነትን መቀበል የፈለገ ማንም ሰው ያለ ኢየሱስ ሊያገኘው አይችልም። ይህ ደግሞ ወደ መመለስ (ንስሐ) እና አቅጣጫን ወደ መቀየር (የሕይወት መለወጥ) ይመራናል። ኃጢአታችንን ማመንና ለእግዚአብሔር መናዘዝን እንዲሁም እግዚአብሔርን ለመከተልና ለመታዘዝ ያለንን ፈቃደኝነት ሁሉ ያጠቃልላል።

ለሙስሊሞች ይህ ሁሉ ትርጉም የለሽ ነገር ነው፤ ምክንያቱም እስልምና (ቁርዓን ሳይሆን) ሰው ‹በንጹህ አንሶላ› ላይ የተወለደና በመሠረቱ መልካም ፍጥረት እንደሆነ ያስተምራል። ሰው የአላህን መመዘኛዎች መጠበቅና ማሟላት ይችላል። ይህንን መጠበቅ በሚያቅተው ጊዜ ወይም ሲሳሳት መልካም ሥራ በመሥራት ጥፋቱን ማካካስ ይችላል።

ከዚህ ባሻገር አንድ ሰው አላህ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ እንደሆነ ተረድቶ ይህን መጠበቅ ይችላል። አላህ ታማኝ የሆነውን ሰው ይቅር ይለዋል።



## ደኅንነት በእስልምና

ይህ በጣም ለየት ያለ ነው። ምንም እንኳ ንስሐ ገብቶ አላህን ይቅርታ መጠየቁ አስፈላጊ ቢሆንም ይህ በአብዛኛው የሚያደርገው፥ አንዳንድ «ትልልቅ» ኃጢአቶች ሲፈጸሙ ነው። ትንንሽ ኃጢአቶች መልካም ሥራ በመሥራት ሊካካሱ ይችላሉ።

ቃሉ (አንድ ጊዜ) በቁርዓን ቢጠቀስም እንኳ፥ ደኅንነት በእስልምና እምብዛም የሚታወቅ ነገር አይደለም።

ሱረቱ 5፡119. አላህ ይላል፡- ይህ እውነተኞችን
እውነታቸው የሚጠቅምበት ቀን ነው።
ለነርሱ በሥሮቻቸው ወንዞች
የሚፈሱባቸው፥ በውስጣቸው
ሁልጊዜ ዘውታሪዎች ሲሆኑ
የሚኖሩባቸው ገነቶች አሉዋቸው።
አላህ ከነሱ ወደደ፤ እነርሱም ከርሱ
ወደዱ፤ ይህ ታላቅ ዕድል (ደኅንነት)
ነው።

ይህ ጥቅስ በግርጌ ማስታወሻ ሲያብራራ፡- «ፋውዝ የሚለውን የዐረቢኛ ቃል፡- ሐሴት፥ ደስታ፥ መከናወን፥ ደኅንነት የምኞት መፈጸም ወይም መሳካት ይለዋል። እንዴት ያለ ግሩም የሕይወት መጨረሻ ወይም የደኅንነት ትርጉም ነው! ይህ እኛ ማግኘት ያለብን የእግዚአብሔር መልካም ደስታ እና ልንደርስበት የሚገባ የእግዚአብሔር መልካም ደስታ በእኛ ፍጹም የሚሆንበት ደረጃ ነው።

«እንግዲህ ይህ ሙስሊሙ ስለ ደኅንነት ያለው ሐሳብ ነው። ይህ ሐሳብ ደግሞ በሌላው ችሮታ ወይም ሥቃይ ኃጢአታችን ካመጣው መዘዝ መዳንን ወይም በሌላው መለኮታዊ መንፈስ ውስጥ ገብቶ መጥፋትን ወይም መዋጥን አያመለክትም፤ ነገር ግን የፍጹም ስብዕና የሥራ ውጤት፥ በውስጣችን የሚያድግ በረከት እና በውጫዊ ነገሮች ላይ ያልተመሠረተ ነገር ነው። ይህንን ለማግኘት ደግሞ ምናልባትም ከፍተኛ የሆነ ጥረትንና የዕድሜ ልክ ወይም ከዚያም በላይ የሆነ ትጋትን ሊጠይቅ ይችላል። ነገር ግን ይህ እጅግ ከፍተኛ የሆነ መከናወን፥ የምኞት ሁሉ ፍጻሜ እና የትም የሌለ ሐሴት ነው።»

«ይህ እኛ ስለ ደኅንነት ያለን ሐሳብ ነው፡- አሉታዊ የሆኑትን የክፋትን ውጤቶች ማስወገድ እና አዎንታዊ የሆነውን ነገር ሁሉ እና ከሁሉም በላይ ልቦቻችን ሊመኙት የሚችሉትን የመጨረሻ ነገር ማግኘት ማለት ነው። ምክንያቱም

የእግዚአብሔር ቸርነትና ልግስና ዓይናችን ካየው፥ ጆሮአችን ከሰማው ወይም በልባችን ልናስበው ከምንችለው ከማንኛውም ነገር ይበልጣል»።

መጽሐፍ ቅዱስን ለሚያውቅና ለሚያምን ለማንኛውም ሰው ይህ በከፍተኛ ደረጃ እግዚአብሔርን መሳደብ ሲሆን፥ ስለ ኃጢአትና ስለ ሰውም ፍጹም የተሳሳተ ሐሳብ ያለው ነው።

እስቲ እናጠቃለው:-

ሙስሊሞች

ስለ እግዚአብሔር

ስለ ሰው

ስለ ኃጢአት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማማ አመለካከት አላቸው።

የእግዚአብሔርን ቅድስናና ጽድቅ በትክክል ካለመረዳታቸው የተነሣ ስለ ኃጢአት ያላቸው ሐሳብ ዝቅተኛ ነው። ይህ ደግሞ ሰው ስለ ኃጢአቱ አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ ይችላል፤ ወይም በራሱ መልካም ሥራ ወይም በራሱ ጥረት እግዚአብሔር ኃጢአቱን ያስወግድለታል፤ ወደሚለው የተሳሳተ ሐሳብ ይመራቸዋል።

ከዚህም የተነሣ ለአንድ ሙስሊም የኃጢአት ስርየት፥ መቀደስ እና መታረቅ ወይምለዚሁ ጉዳይ የጸጋ አስፈላጊነት አይታየውም።

አሁን እንግዲህ ሙሊሞችን በወንጌል በመድረሱ ጉዳይ ላይ በጠቅላላ ልዩ የሆነውን አመለካከታቸውንና ልምምዳቸውን ማጤን እንደሚያስፈልግ መረዳት ጀምረናል።

እስቲ መጽሐፍ ቅዱስን፥ ወንጌልን፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ማለትም እግዚአብሔርን ሙስሊሞች እንዴት እንደሚመለከቷቸው እንይ። ከዚያም በዚያው መሠረት ያለውን የክርስትናን መልእክት እንመልከት።

ሙስሊሙ እኛን የሚረዳን እኛ እርሱን በተረዳነው መጠን ነው

እኛ በጀልባ ውስጥ ሆነን አንድ በውኃ ውስጥ እየሰመጠ ያለን ሰው ለማዳን ብንፈልግ፥ ወደ ሰውዬው ዘንበል ብለን እጃችንን የቻልነውን ያህል መዘርጋት አለብን። ነገር ግን ይህን እያደረግን ሳለ እኛ ራሳችን ሚዛናችንን ጠብቀን በአስተማማኝ ሁኔታ ጀልባው ውስጥ መሆናችንንም ማረጋገጥ አለብን። እኛ ራስችን



የምንወድቅ ከሆነ ግን የሚሰምጠውንም ሰው ሳንረዳው ዓላማችንም ሳይፈጸም ሁሉም ከንቱ ሆኖ ይቀራል።

(ምሳሌው በዶ/C ደብልዩ ባክበርግ የተነገረ ነው።)

ስንቱ ብርቱ የተባለው ክርስቲያን ይሆን አንድን ሙስሊም ለማስረዳት ዘንበል ብሎ እጁን ሲዘረጋ የራሱን ሚዛን መጠበቅ አቅቶት በአሳዛኝ ማጥ ውስጥ ያልወደቀ! አንዳንዶቹን መመርመር አለብን። አብዛኛውን ጊዜ አንዳንድ ፈጣን የሆኑ «ውጤቶች» ማንኛውንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ሥን-መለኮታዊ መረዳቶችን የማይታወሙ፥ የአንድ ዘዴ መልካምነት ማረጋገጫ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ።

## ለሙስሊሞች ወንጌልን ለማድረስ ቁርዓንን መጠቀም

በግልጽ እንደሚታወቀው ሙስሊሞች ቁርዓንን ሲቀበሉና ሲያምኑበት መጽሐፍ ቅዱስን ግን አይቀበሉም። ይህ እውነት ደግሞ አንድ ሰው ኢየሱስን ለማሳየት ቁርዓንን መጠቀም አለበት ወይ? ወደሚለው ጥያቄ ያመራናል። በእርግጥ በቁርዓን ውስጥ ስለ ኢየሱስ መልካም ነገር የሚናገሩ ብዙ ጥቅሶች አሉ። እንዲያውም አንዳንድ ክርስቲያኖች የኢየሱስን ስቅለትና ሞት በቁርዓን ውስጥ ለማረጋገጥ ይዳዳቸዋል። በእርግጥ በጥሩ የክርስቲያን መጽሐፍ ተንታኝ ታይቶ ካልተተረጎመ በስተቀር ቁርዓን ይህን አያስተምርም። ይህስ ምን ያህል ተገቢ ነው?

> «የቁርዓን ተንታኝ የሆነ ክርስቲያን በብዙ ነጥቦች ላይ በቁርዓንና በመጽሐፍ ቅዱስ መሐል ጠቃሚ የሆነ ስምምነት እንዳለ አድርጎ ሊመለከት ይችል ይሆናል። ይህን በማድረጉ ሙስሊም ሆነው ጥያቄ ለሚጠይቁና ከእስልምና ለተለወጡ ክርስቲያኖች እንዲሁም ከእስልምና ለተለወጡ አብያተ ክርስቲያናት የትኛውን መጽሐፍ እንደ ባለ ሥልጣን መቀበል እንዳለባቸው ሳያውቁ ሊምታታባቸው ይችላል።»
>
> «እውነቱ ግን ለክርስቶስ ራስን መስጠትንና ያለ ጥርጥር በመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን መገዛትን ያጠቃልላል። ጥያቄ የሚጠይቅ አንድ ሙስሊም በመጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ከተናገራቸው ነገሮች ጋር ፊት ለፊት ከተገናኘ በኋላ አንድ ምርጫ ይኖረዋል:- ወይ ቁርዓንን ትቶ ራሱን ለመጽሐፍ ቅዱስና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ካለው አመለካከት መስጠት፥ ወይም ለቁርዓንና ቁርዓናዊ ለሆነው የክርስቶስ ሐሳብ ራሱን ሊያስገዛ ይችላል» (ሳሙኤል ስኩሉርፍ:- «ወንጌልን ለሙስሊሞች በማድረስ ውስጥ የቃሉ ትንተናና አተረጓጎም ችግር›።»

ምናልባት አንድ ክርስቲያን በተገቢው መንገድ አንድን ሙስሊም የሚያምንበት መጽሐፍ የሚያዘውና የሚገልጠው ‹የቀድሞው መጽሐፍ› (መጽሐፍ ቅዱስን ማለት

ነው) ስለ ኢየሱስና ስለ ሌሎች ነገሮች የሚናገረው መልካም ነገሮች አሉት ብሎ ሊያሳስበው ይችላል። ሆኖም ቁርዓን ልክ አይደሉም የሚላቸውን ሐሳቦች ለመቀበል ግን በጣም ያስቸግረናል። («እስልምና ስለራሱ ያለው አመለካከት፥ ሌሎች ያላቸው አመለካከትና ምንነቱ» ከገጽ 75 ጀምሮ ተመልከት)፤ ወይም አስቀድሞ ስለተወሰነ ዕጣ ፈንታ (ከገጽ 93 ጀምሮ) አንዳንዶች፥ እንዳደረጉት እኛም ሙሉ በሙሉ «ከቁርዓን ኢየሱስን ከመስበክ» መቆጠብ አለብን። ቁርዓን ለአንድ ክርስቲያን ምንም ዓይነት ሥልጣን አይሰጠውም! ብዙ የምናገናዝበው ነገር ቢኖርም ይህንን ግን ግልጽ ማድረግ እንፈልጋለን!

## የዐረብኛ አባባሎችን የአጠቃቀም ዘዴ

በምንደርሳቸው ሰዎች ማንነት መሠረት፥ ዐረብኛን የመጠቀሙ ነገር በጣም አስፈላጊ ነው። ዐረብኛ በማይናገሩ ሀገሮች እንኳ ሳይቀር፥ ሙስሊሞች የዐረብኛን ቋንቋ ተምረዋል፤ እየተማሩም ነው። ምክንያቱም ሁሉም ሃይማኖታዊ አባባሎች በዐረብኛ ስለሚሰጡ። ስለዚህ እነዚህን ከነትርጉማቸው ማወቁ አንድን ነገር ለማብራራት ስንፈልግ ስለምንጠቀምበት በጣም አስፈላጊ ነው።

ነገር ግን በኋላ እኛ ፍጹም ያለመሆናችንን ለሙስሊሙ የማሳየቱ ጉዳይም መኖር አለበት። ምናልባት ‹ከፍተኛ ኃይል ያለው ትኩስ ወንጌለኛ› ብለው ሊሰይሙን ይችላሉ፤ ነገር ግን እኛ የነሱን አመለካከትና ሐሳብ አንዳንድ ቃላቶቹን እስከ መማር ድረስ ለመገንዘብ እንደምንፈልግ ልናሳያቸው ይገባል። ይህ ምናልባት ደስ የሚያሰኝ ሊሆን ይችላል።

ቢሆንም ቅሉ እኛ ምን እንደምንሠራና እንዴት እንደምንሠራ ማወቅ አለብን። ያለዚያ ግን ወይ መሳለቂያ የሚሆን ውጤት እናጭዳለን፤ ወይም ምናልባት በደንብ የተማረ ክርስቲያን ሚስዮናዊን እንደሚፈሩ እኛም እናስፈራቸዋለን። እስቲ ይህንን በምሳሌ ላብራራው፡-

አንድ ሚሲዮናዊ ከጥቂት ሙስሊሞች ጋር ሲነጋገር ኢየሱስ ክርስቶስን ‹ነቢ ዒሣ› (ነብዩ ወይም መልእክተኛው ኢየሱስ) እያለ ይናገር ነበር። ሐሳቡ ‹እንግዳ› የሆነ አባባል ላለመጠቀም ለነሱ እንዲገባቸው ብሎ እንደሆነ ጥርጥር የለውም። በመጨረሻ አንዱ ሙስሊም ትከሻውን ያዘውና የተናገረውን በማረጋገጥ ሁኔታ «ኢየሱስ ከነቢይ የበለጠ እንዳልሆነ የተቀበልክ የመጀመሪያው ክርስቲያን አንተ ነህ!» አለው። ስለዚህ እንዲረዱት ያደረገው ጥረት ሌላ እሳት ቆሰቆሰ።

ሙስሊሞች፡- በክርስቲያኖች የሚደረግን የሃይማኖት ማስለወጥ ለማስቆም፥ ሙስሊም ያልሆኑ ሁሉ በዐረቢኛ እንዳይጠቀሙበት ማድረግ ጀምረዋል። በእርግጥ በማሌዥያ ያሉ ሙስሊሞች «ሙስሊማዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶችን የመቆጣጠርና



የማገድ ማስታወቂያ 1989 (እ.ኤ.አ.)» እንዲወጣ ማድረጋቸው አንድ ነገር ነው። ይህ ማስታወቂያ ሙስሊም ያልሆኑትን ሰዎች ሙስሊማዊ ምንጭ ያላቸውን አገላለጾች ማንኛውም ሙስሊማዊ ያልሆነ የሃይማኖት ነገር በተመለከተ በመግለጽ ሊጠቀሙባቸው እንደማይቻል የሚገልጽ ነው። እንደ ‹አላህ› እና ‹ራሱል› ያሉት ቃላት በዚሁ ምድብ ሥር ያሉ ናቸው። አል-ኪታብ በመባል የሚታወቀው በማሌዥያ ቋንቋ የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ አላህን (ለእግዚአብሔር)፥ ራሱልን (ለነቢይ) የመሳሰሉ ቃላትን ስለተጠቀመ ከ 1981 ጀምሮ ታግዷል («ኤስ.አይ.ኤም ናው» ከሴፕቴምበር እስከ ኦክቶበር 1989)።

እንግዲህ የዐረብኛ አባባሎችን ስንጠቀም መምረጥ እንዳለብን ተመልክተናል። ‹ኢንጂል›ን ለወንጌል እንዲሁም ‹ነቢ ዒሣ›ንም፥ ‹ሙሳ›ን ወይም ‹ኢብራሒም›ን መጠቀሙ ከተራና ከተለመደው የአጠቃቀም ሁኔታ እንደማያልፍ መገንዘብ አለብን።

## ክርክርና የኑሮ ዘይቤ

አንድ ክርስቲያን መስካሪ ድካሙ ሁሉ በጣም ጥቂት ተፅዕና እንዳለው ካስታወሰ ወይም በጣም ጥቂት ውጤት ብቻ የሚያስገኝ ከሆነ ሁለት አማራጭ ዘዴዎች አሉት። ሁለቱም የተመሠረቱት አንድ ሙስሊም የወንጌልን አስፈላጊነትና ጥቅም እንዲረዳ ከልብ ከመመኘት የተነሣ ነው።

አንድ ሰው እምነትን በተጨባጭ ማስረጃዎች የመግለጡን፥ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የማብራራቱን፥ መንፈሳዊ ይዘት ያለውን ነገር ማወጅንና መግለጽን ወደ ግጭቶች ወይም ውዝግቦች ያመራል ብሎ ይደመድማል። በመሆኑም ስለ መንፈሳዊ ነገሮች የሚደረጉ ክርክሮች ሁሉ ከንቱ ስለሆኑ፥ መቅረት አለባቸው ብሎ በማሰብና በግልጽ የሚታየውን አቀራረብ በመምረጥ፡- እስቲ በሙስሊሞች መሐል እንኑርና ክርስቲያናዊ ፍቅራችን፥ ቸርነታችን እና ትሕትናችን ራሱ ይናገር! በማለት ያስባል።

ክርክርንና እምነትን በተጨባጭ ማስረጃዎች መግለጽን ትተን ሙስሊሞችን በትሕትናና በፍቅር በአኗኗራችን ወደ ክርስቶስ ለመሳብ እንድንሞክር የሚያነሳሳን አመለካከት የተመሠረተው ሙስሊሞች እንደ ክርስቲያኖች ያስባሉ፤ እንዲሁም ይኖራሉ ብለን ስለምናስብ ነው። ይህን ስንል ደግሞ አንድ ሙስሊም በሚወዱትና በሚጠነቀቁለት አይሳብም ለማለት አይደለም! ነገር ግን ፍርሃት የተሞላበት ምስክርነት በሙስሊሙ ዐይን ደካማነትን ያስረዳል። በግልጽ ለመናገር ባይፈልግም እንኳ፥ ደካማነት የሚናቅ ነገር ነው። የራሱን አቋም ጠንካራነት በመገንዘብ ራሱንና እስልምናን እንደ ድል አድራጊ አድርጎ ይቆጥራል። የክርስትና ሕይወት ዘይቤ ግልጽ የሆነ በቃል የሚነገር ምስክርነት ከሌለበት በፍጹም ምስክርነት ሊባል አይችልም፤

ምክንያቱም ይህ ሁኔታ አንድ ሙስሊም በክርስቲያኑ ላይ የእስልምናው ተፅዕኖ ፍሬ ማፍራት እንደጀመረ አድርጎ እንዲያስብ ሊያደርገው ይችላል።

ሆነ ብሎ ከአንድ ሙስሊም ጋር ክርክር የመጀመሩ ጉዳይ ምንም ጥበብ የለበትም! ሆኖም ግን ይህን ነገር ባመዛኙ ያለኪሣራ ልንጠቀምበት አንችልም። ሙስሊሙ ለእምነቱ ቆሞ በሚመሰክርበት ጊዜ፥ ከክርስቲያኑም በኩል በራሱ እምነት ላይ ያለማወላወል ቆሞ ማየትን ይጠብቅበታል።

## ወንጌልን ከአካባቢው ጋር የማስማማት ሂደት

ይህ ጥረት ወንጌሉ የሚደርሳቸው ሰዎች በአንዳንድ ማኅበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ምክንያቶች እንግዳ ሆኖባቸው ወንጌሉን እንዳይቃወሙት ለማድረግ የወንጌሉን ቅርፅ አንዳንዴም ይዘቱን ጭምር ለማለዘብ የሚደረግ ሙከራ ነው። ሐሳቡ የመጣው ከቅኝ አገዛዝ ዘመን በኋላ በተፈጠረው አዲሱ ብሔራዊና ባህላዊ ንቃተ ኅሊና በሰረጸበት ጊዜ ነው። ማንኛውም የውጪ ሀገር ተፅዕኖ እንዳለበት የሚገመት ነገር ሁሉ ወንጌልንም ጨምሮ በጥርጣሬ ዓይን ይታይ ነበር። ብሔራዊ የማነቃቃት ሄደት ከዚያው ሃይማኖታዊ መነቃቃት ጋር ጎን ለጎን ተጉዟል። ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ተቃውሞ ከመድረሱ በፊት አንዳንድ ስለ ሚሲዮናዊነት ያጠኑ ሰዎች እንደሚሉት ወንጌሉን ‹አገርኛ› የማድረግ ወይም ከባህሉ ጋር የማቀናጀቱን ሙከራ ተያያዙት። የአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ቅርጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከመሆኑ ይልቅ የምዕራባውያንን ባህል የሚያንፀባርቅ እንደነበረ የሚዘነጋ አይደለም። በዚህ ማስረጃነት ሾጣጣ የሆኑ የቤተክርስቲያን ሕንፃዎችን፥ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር አወቃቀሩን፥ የቅዱስ ቁርባን ሥርዓቱን ወይም የተወሰነ ባህልን የሚያሳዩ መዝሙሮችን መመልከቱ ይበቃል። በተጨማሪም አብዛኛው ነገር ሚሲዮናውያኑ ከመጡበት ሀገር ታሪክና የኑሮ ዘይቤ ጋር ይመሳሰላል። በእርግጥ በዚያን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን በአፍሪቃ፥ በእስያ ወይም በደቡብ አሜሪካ የኑሮ ዘይቤና ሁኔታ መሠረት ለማጥናት አስቸጋሪ ነበር፤ ምክንያቱም በሀገሩ ዘይቤ መሠረት መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም ያለባቸው የሀገሩ ሰዎች ብቻ ሲሆኑ ይህም የሚሆነው ምዕራባውያኑ አስተማሪዎች ቃሉን በደንብ አስተምረዋቸው ከተመሠረቱበት በኋላ ነው።

አሁን ግን ስለ ሚሲዮናዊነት ጥናት ያደረጉ ሰዎች እንደሚሉት ያንን ሁሉ ለመቀየር አሁን ጊዜው ደርሷል። ሁልጊዜ በዚህ ነገር ውስጥ ትኩስና የሚያነቃቃ አዲስ ሐሳብና ልምምድ ቢኖርም፥ ግን ዘመን ባለበት ቆሞ እንደማይጠብቀን ሳናስተውል እንቀራለን።

በመሠረታቸው ሙስሊማዊ የሆኑ የሥርዓት ዓይነቶች፥ (ምናልባት አስቀድሞ ከነበሩት ከአይሁድና ከክርስቲያን አምልኮ የተወሰዱ ሊሆኑ ይችላሉ፤) ‹የዒሣ



ተከታዮች› (ለክርስቲያኖች) ክርስቲያናዊ መልክ ያለውን፥ ዓርብ የሚደረገውን ‹ጸሎት› ማለትም ‹ሰላት› ለማድረስ፥ ሥርዓታዊ የሆነውን መታጠብ (ውዱእ) ከፈጸሙ በኋላ በሚገናኙበት በ ‹ዒሣ መስገድ› (ለ በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ገብተዋል። በግልጽ እንደሚታወቀው ራሳቸውን በመሸፈን ሙስሊማዊ የሆነውን በግንባር ተደፍቶ የመስገድ ሥርዓትን ይከተላሉ። እንዲያውም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብን በዐረብኛ እየደገሙ ያዜሙ ይሆናል! በረመዳን ጊዜ ከሙስሊም ጎረቤቶቻቸው ጋር ‹በመተባበር› ጾሙን በሙሉ ወይም በከፊል ሊጾሙ ይችላሉ።

በእርግጥ ይህ ፍጹም ሙስሊማዊ ነው የሚለው አመለካከት ባይኖርበት ኖሮ፥ በመጾሙ፥ በፀሎት ጊዜ ተደፍቶ በመስገዱ፥ እንዲያውም ይህንን ከማድረጉ በፊት በመታጠቡም ጭምር ምንም ስሕተት የለበትም።

ከዚህ ጎን ለጎን ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችና ድርጊቶች የሚገልጹት ምሳሌያዊ ነገር እና ትርጉም እንዳላቸው ልናስተውል ያስፈልጋል። ብዙ ከእስልምና የተለወጡ ሰዎችን ይህን ጉዳይ እንዴት እንደሚመለከቱት ጠይቀናቸው ነበር። መልሳቸውም ሁልጊዜ ይህ አድርባይነት እንዲያውም ሃይማኖቶችን ማደበላለቅ ነው የሚል ብቻ ነው።

እንግዲህ ይህን ዓይነቱን አቀራረብ ሙስሊሞች እንዴት ነው የሚመለከቱት?

## ከአካባቢው ጋር ስለ ማቀናጀት ሙስሊማዊው አመለካከት

ሐምሌ 1987 እ.ኤ.አ. በተጻፈው «የስልምና ጆርናል (መጽሔት)» ላይ «ክርስቲያንን ሙስሊም የማድረግ ሂደት» በሚለው ርዕስ ሥር ስንመለከት የሚከተሉትን እናነባለን

> «ከአካባቢው ጋር የማስማማት ሂደት ላይ ላዩን ሲያዩት ሰዎችን ለመሳብ የሚደረግ የማታለያ ልመና (ጸሎት) ይመስላል»።

«ነገር ግን ጠለቅ ያለውን ሂደት ስንመለከት በእስልምና ዓምዶች ያሉትን ድርጊቶች ለማቀፍ ሲባል የክርስትና ልምምዶችን ወደጎን መተውን ያጠቃልላል። ፀሐፊዎቹ የሚደግፉትንና የሚናገሩትን ስንመለከት ወንጌልን ከአካባቢው ጋር የማስማማት ሂደት ጠለቅ ያለ መዋቅር በግልጽ ያሳየናል።»

«ዶክተር ዝውሜር የተባሉት የቀድሞ ሚሲዮናውያን በእስልምናና በሙስሊሞች ላይ መጨረሻ ስለሌለው ኩነኔና ነቀፌታ ጽፈዋል። አዲሶቹ ሚስዮናውያን ግን «የአድርባይነቱን» ቦታ ይዘዋል። ያለምንም ሐፍረት ጸሐፊው ‹ያለ አድርባይነት እኛ በእስልምና ያለውን መልካም ነገር ማድነቅ እንችላለን› ብሎ መጻፍ ይችላል። የነርሱ

አቋም የሚደከመው ከአሻፈረኝነት ወደለዘብተኝነት ሲመጣ ነው። የሚቀጥለው ደረ
እስልምናውን እንዳለ መቀበል ነው»›

«ጸሐፊው ስለ ሙስሊሞች ለማለት የተገደደው ነገር አለ፤ «እነርሰ
ከሚከተሏቸው ውስብስብ ሃይማኖቶች ሥርዓቶች ይልቅ ክርስቲያኖች የሚከተሏቸወ
የላቁና የሚበልጡ መሆናቸውን ማመን አለባቸው። ምክንያቱም ክርስቲያኖቹን፥
እግዚአብሔርን እንዲያውቁ ያደረጉዋቸው እነዚህ ሥርዓቶቻቸው ናቸውና»። ይ
የተጋነነ ንግግር ነው፤ ነገር ግን እስቲ እውነተኛውን ልምምድ እንመልከት፡
ጥምቀትን መተው፥ የረመዳንን ጾም መጾም፥ እና የሙስሊም ልብሶች መልበስ፥
እንዲሁም የእስልምናን እውነተኛነት አስረግጦ መናገር። ምናልባት ጸሐፊው እን
አብዛኞቹ ሚሲዮናውያን፥ እነርሱን እግዚአብሔርን እንዲያውቁ የረዳቸው ሥርዓ
ከክርስቲይናዊ ባህል ይልቅ ከቁርዓንና ከሱና እንደሆነ የተገነዘበ ይሆናል፥
ምናልባትም ደግሞ ጸሐፊው እና ክርስቲያን ሚሲዮናውያኑ፥ ማታለል የሞላበት
«ከአካባቢው ጋር የማስማማትን ዘዴ» አላህ ሙስሊም የማድረግ ሂደቱ
እየተጠቀመበት እንደሆነ ይገነዘቡ ይሆናል። ‹አላህ ከዕቅድ አውጪዎች (
«ከመሐንዲሶች») ሁሉ በላይ ነው (ሱረቱ 3፡47፤ 8፡30)።

ይህንን ስናጠቃልለው የሚቀረን አማራጭም፡-

## ፊት ለፊት መጋፈጥ አስፈላጊ ነው

የክርስትናን መልእክት ከእስልምና ይልቅ ምን ያህል ገናና እንደሆነ ማቃረ
ግዴታችን ነው። ይህንንም በምናደርግበት ጊዜ የእስልምናን ምንጭን ከነ ሥ
ጉድለቱን ማፍረጥረጥ ይኖርብናል። ይህ ነገር መቼና እንዴት መደረግ አለበ
የሚለው ጥያቄ በጣም አንገብጋቢ ነው። ነገር ግን ይህን አለማድረጉ ደግሞ ሙስሊ
የክርስቶስ ክፍል ለመሆን ከእስልምና ፊቱን መመለስ እንዳሌለበት፥ በልቡ በጭራ
እንዳያምን ማድረግ ማለት ነው። ይህ ደግሞ እንደነ ሐዋ. 17፡22 እና 1 ቆሮ. 9፡1
ባሉት ክፍሎች የሚደገፉ አይሆንም።

እስቲ ፍራንሲስ ሼፈር በዚህ ነጥብ ላይ የተናገሩት ልጥቀስ፡-

«እውነት በውስጧ መጋፈጥን ትይዛለች። እውነት መጋፈጥን ይጠይቃል፤
ምንም ቢሆን በፍቅር የሆነ መጋፈጥ እውነተኛ መጋፈጥ ነው። ድርጊታች
ሁልጊዜ እውነትን ሳይጠብቅ ሁሉን የሚያስተናግድ ከሆነ፥ አንድ ችግር አ
ማለት ነው። ልክ ቅድስና ብለን የምንጠራው ነገር ያለ ፍቅር የእግዚአብሔ
የሆነ ቅድስና እንዳልሆነ ሁሉ፥ እንዲሁ ያለ ቅድስና ፍቅር ብለን የምንጠራወ



ነገር የእግዚአብሔር ፍቅር ልንለው አንችልም። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፤
እንዲሁም እግዚአብሔር ፍቅር ነው።»

(«ታላቁ የወንጌል አማኞች ጥፋት»)።

በዚሁ ዘመን ፊት ለፊት መጋፈጥ ተቀባይነት እንደሌለው በሁላችን የታወቀ ነው። ዳሩ ግን የክርስቲያን አእምሮ እንኳ ሳይቀር በዚሁ ዓለም ፍልስፍና ተማርኮ ማየቱ የሚያስገርም ነገር ሆኖአል። እርግጥ ነው፥ በዚህ ዓለም ፍልስፍናና በኃይማኖት አስተሳሰብ የተጋለጥን ሰዎች ሆነን ሳለን ከእኛ መሐል «እኔን አይነካኝም» ሊል ማን ይችላል? ብለን ልንጠይቅ እንችላለን። አዎን፤ በአንድ በኩል ለዘብ ባለ ሁኔታ የዓለም አስተሳሰብና ፍልስፍና በመጠኑ ተቀባዮችና አድማጮች መሆን ይኖርብን ይሆናል፤ በሌላው በኩል ግን የሚባለውን ሁሉ መቀበሉም ደግሞ ስሕተት ነው። በዚህ ነጥብ ላይ የመጽሐፍ ቅዱሳችን አቋም በጣም ግልጽ ነው።

ምንም እንኳ የአክአብና የኤልዛቤል ቁጣ የሚያጠፋው መስሎ ቢመጣበትም፥ ኤልያስ አራት መቶ የበዓል ነቢያትን በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ተጋፈጣቸው። እንዴት እንደሚተባበራቸው ወይም በእስራኤል ስላለው የአምልኮ ሁኔታ እንዴት በጋራ እንደሚፈጽሙት ሻይ እየጠጡ ለመወያየት ወደ እነርሱ አልሄደም። ሁኔታው በውሸት ላይ እውነትን ይዞ ፊት ለፊት መጋፈጥ ነበረ!

## ጥያቄ ስለ እውነት

ከሙስሊሞች ጋር በምናደርገው ንግግር ከሁሉ በፊት ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሰው እንዲሁም ሁለቱ ስላላቸው ግንኙነት እውነቱ ምን እንደሆነና የት ላይ እንደሆነ ለመግባባት መንገድ መፈለግ አለብን። እንዲሁም እውነትን መፈለግ ነገርችን በጥንቃቄና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለማሰብና በዝርዝር ለመመልከት የሚያስችለን የመጀመሪያውና ጠቃሚ የሆነ ዓላማችን ነው። ይህ ነገር በሙስሊሙ ዘንድ የተለመደ አይደለም ሲባል ደግሞ አንድ ሰው እነዚህን መነሻ ሐሳቦች ጭራሽ መተው አለበት ማለት አይደለም። በተቃራኒው፥ ሙስሊሙ እግዚአብሔር የሰጠውን ምቹ ሁኔታዎች ተጠቅሞ እውነቱን ከስሕተት እንዲለይና መለኮታዊው መገለጥ የቱ እንደሆነ ተረድቶ እንዲመርጥ ልናደፋፍረውና ልንገፋፋው ይገባል።

ግጭትንና ውዝግብን ለማስወገድ የመሞከሩ ሁኔታ ሙሉ የሆነ ግንኙነትን ወይም መግባባትን ሊያግድ ይችላል። እንደሚታወቀው ሁሉ ግልጽ የሆነ እውነት ከሌለ በስተቀር ምንም ሊሠራ አይችልም።

## ያለ መግባባትን የማስወገጃ ዘዴ

ፍቅር ሁለት ነገሮችን እንድናደርግ ያስገድደናል:- የመጀመሪያው ሌላውን ያለምንም ጥላቻ/ቅሬታ እቀበለዋለሁ፤ ሁለተኛው ስለ እርሱ ብዙ ነገር እማራለሁ፤ ከዚያም በኋላ ወንጌልን እርሱ ራሱ ሊገነዘበውና ሊረዳው በሚችለው መንገድ ከእርሱ ጋር ላዛምደው እችላለሁ። ተራ የሆነ ውጫዊ መቀራረብ ፍቅር አይደለም!

በጂሚ ስዋገርት (አሜሪካዊ ሰባኪ) እና በሙስሊሙ ተቀናቃኝ በአሕመድ ዲዳት መካከል በሕዝብ ፊት በተደረገው ክርክር፥ የተጨነቀ የሚመስለው ስዋገርት በመሐመድ ላይ የክርስቶስን የበላይነት ለማሳየት ሌላው አልሆን ሲለው አንድ ታሪክ ተጠቅሞ ነበር:- በአንድ ቦታ በሚሲዮናዊነት ተግባር ላይ ሳለ አንድ ሙስሊም ታመመ። የእስልምናው መሪ የሆነ ሰው ለታመመው ሰው «በመሐመድ ስም» ፀለየለት፤ ነገር ግን አልዳነም። ከዚያም አንድ ክርስቲያን ሚሲዮናዊ በኢየሱስ ስም ጸለየለትና ተፈወሰ!

ይህ ነገር ለድል አድራጊነት የማያስፈልግና የማይጠቅም ከመሆኑም በላይ በሙስሊማዊ የፕሮፓጋንዳ ማዕከል የተዘጋጀው የቪዲዮ ፊልም ላይ እንደተጨማሪ ማስታወሻ «በትክክለኛና በእውነተና መንገድ ማንም ሙስሊም በመሐመድ ስም አይጸልይም» ተብሎ እንዲጻፍ ተደርጎ ነበር። ይህ ነገር ባጭሩ ክርስትና እስልምናን የሚባል ተራ አባባል ነው።

ይህ በመባሉ ግን ለዲዳት የድል ቀን ሆነለት። ተቀናቃኙን እንደ ውሸታም አጋልጦታል፤ (ውየም ምንም እንኳ ሆን ተብሎ የተደረገ ቢሆንም ቢያንስ ቢያንስ ውሸትን እንደሚደጋግም ሰው አድርጎ አቅርቦታል)።

እዚህ ላይ ችግሩ ሁለት መልክ አለው። ክርስቲያኑ ተከራካሪ ለዚህ ሁኔታ አልተዘጋጀም፤ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። እንዲህ ዓይነት ጭፍን የሆነ ስሕተት ከመሥራቱ በፊት ስለተቀናቃኙ ሃይማኖት ብዙ ማወቅ ነበረበት። ከዚህም በተጨማሪ ያቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ በሙስሊሞች ዘንድ ይቅርና በክርስቲያኑም ዘንድ በይዘቱ ያልዳበረና ውስንና ተቀባይነት የሌለው ነው።

እነዚህ ቪዲዮዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ታይተዋል። ከተናጋሪው አፍራሽ ምስክርነት ሌላ በክርስትና ላይ በቀላሉ የማይታይ ጉጂ የመከራከሪያ በር ከፍተው እንዳለፉ መገመት ይቻላል።

ለሙስሊሞች ያለን ፍቅር ሁልጊዜ ባለን ታማኝነት መገለጽ አለበት፤ በተጨማሪም በእውቀትና በግንዛቤ ብስለት መጠናከር አለበት።



## ሙስሊሞችን መረዳት

አንድን ሙስሊም ለመረዳት አስቀድመን እስልምናን ልንረዳ ይገባናል

### እስልምና ራስን ማስገዛት ማለት ነው

እስልምና የፈለገው ነገር ቢሆን ለአላህ ፈቃድ፥ ለኢማኑ እና ‹ለዲኑ› እንዲሁም ብዛት ላላቸው የሱናትን አመለካከቶች መገዛት ነው። ይህ ደግሞ የእስልምናው ሕብረተሰብ በሌላ የአካባቢ ሁኔታ የሚኖር ከሆነ ልዩ መታወቂያ እንዲኖረው እና የማይለወጥ አጠቃላይ የሆነ የአስተሳሰብ አጥር በሕብረተሰቡ ዙሪያ እንዲኖር ወደ ማድረጉ ደረጃ ያመራል። ይህ አጥር እስልምናን በውስጡ ከሚካሄዱት ነገሮች ሁሉ ጋር በመጠበቅ፥ ሌላውን ሁሉ በውጪ ለማስቀረት የሚያገለግል ነው። ማንኛውም የምስክርነት ቃል ያለው ክርስቲያን እንደ አገልጋይ ይታያል፤ ይህ ቃል ደግሞ ተከላካይነታቸውን ወይም አለመቀበላቸውን ሲጨምር የመታመናቸውን ዕድል ይቀንሳል። ይህ የሚሠራው በአንዳንድ ማኅበራዊ ነክ (ሶሲዮሎጂካል) መመሪያዎች መሠረት ነው። እስቲ እነዚህን እንመልከት:-

እስልምና ለ መገዛት

ሙስሊም ለ ራሱን የሚያስገዛ

ስርወ ቃሉን ብንመረምር ሰላም ከሚለው ቃል ባር ዝምድና እንዳለው እንረዳለን።

በክፍል 1 ስለ እስልምና ተጨባጭ የሆነ ግንዛቤ አግኝተናል። በመሠረቱ ሙስሊሞች ስለዚህ ጉዳይ ስሜታዊ የሆነ ግንዛቤ ነው ያላቸው።

### «በፍጹማን» መካከል ያለ ውዝግብ

የሁሉ ራስና ፈጻሚ ማነው?

ለአንድ ክርስቲያን በማንኛውም ነገር ላይ የመጨረሻው ባለሥልጣን እግዚአብሔር ነው። በዚህ ቦታ ላይ በይበልጥ በግልጽ ለማለት የፈለግነው ያህዌ ኤሎሔን፥ የእስራኤልን አምላክ፥ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት ነው። በፍጥረት እና በታሪክ ውስጥ ከምናውቀው ባሻገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምናገኘው መሠረት፥ የክርስቲያን የመጨረሻው ባለሥልጣን እግዚአብሔር ነው። ከዚህ የተነሣ ሰው፥ ከእግዚአብሔር ጋር ሊታረቅ የሚችልበትና ከኃጢአቱ የሚነጻበት ብቸኛ መንገድና አማራጭ ክርስቶስ ነው።

ለአንድ ሙስሊም የመጨረሻው ባለሥልጣን በቁርዓን ላይ እንደተገለጸው አላህ ነው። እስልምና ደግሞ የአላህና የመሀመድ ሃይማኖት ነው። መሐመድም ቁርዓንና ትርጉሙን ከአላህ ዘንድ የተቀበለ እንደሆነ ይታመንበታል።

ፕሮፌሰር ክላውስ ኑርንበርገር እንደሚሉት ከሆነ እነዚህ ሁለት ሥልጣናት ሊታረቁ ከቶ አይችሉም። የሰውም አእምሮ ምንም ያህል ቢመራመር አይደርስባቸውም። እንደ ፕሮፌሰሩ አነጋገር ከሆነ ፍጹም የሆነው ነገር (መለኮታዊ እውነት ማለታቸው ይመስላል) በሰው ልጅ ሊፈጠር ወይም ሊፈለሰፍ አይችልም። ነገር ግን እውነትነቱ በሰው አእምሮ ይገዘፍና (ይጎላና ) ያ- በእርሱ የተማረከውን ሰው እንደ ፍጹም እውነት አድርጎ እንዲቆጥረው ያደርጋል።

በተጨማሪም ፕሮፌሰሩ፡- ሥነ መለኮታዊ ምግባር በተባለ ጥናታዊ ጽሑፋቸው የሚከተለውን አስፍረዋል።

‹የሰውን ኀሊና እንደ ትግል ሜዳ በመጠቀም የተለያዩ ‹ፍጹም-እውነቶች› ፍልሚያ ያካሂዳሉ። የሰውንም አእምሮ ይሞግታሉ። ሰውም የበለጠ ኃያል ለመሰለው እውነት መገዛት ግድ ይሆንበታል። ያ እውነት ስር ሰዶ የተመሠረተ ከሆነ - ከእርሱ የበለጠ ሌላ እውነት መጥቶ መሠረቱ ካልተናወጠ በስተቀር ሰው ስለ እሱ ያለውን ጥርጥሩንና ጥያቄውን ያቆማል። እስከተወሰነም ጊዜ ድረስ ዘላቂና አስተማማኝ መስሎ ይቆጠራል።»

‹ፍጹም እውነት› ብለው የያዙት ነገር ወይም እንዲሁም መረዳት በአንድ ሰው ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ሙሉ በሙሉ እንገነዘባለን። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ሃይማኖታዊ ወይም ፖለቲካዊ ለሆነው ከፍተኛ እውነታቸው በድፍረትና በሙሉ ፈቃደኝነት እንደተሰዉ በታሪክ ተመዝግቧልና።

ፍጹም እውነት ተብሎ የተያዘ ነገር ለግለሰብም ሆነ ለቡድን ዓላማና ትርጉም የሚሰጥ ነገር ነው። የቡድኑ የመቀራረብ ደረጃ ጠንካራ ከሆነ፥ ‹የፍጹም እውነታቸውም› ተፅዕኖ በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ ጠንካራ ይሆናል። ይህ ነገር በተለይ ለሙስሊሞች እውነት ነው።

ፕሮፌሰር ኑርንበርገር የጋራ የሆነውን ውጤት እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል፡-

ቡድኖች . . . «እርስ በርስ የመቀባበልና የመወዳጀት መንፈስ አላቸው። ሁሉም ሰው መሆን የሚፈልገውን የመሆን፥ መሥራት የሚፈልገውን የመሥራት፥ የሚደሰትበትን ነገር የመምረጥ መብት እንዳለው የሚያረጋግጥለትን ዋስትና ይፈልጋል። የመኖር መብቱ ካለበት ቡድን ውስጥ ተሰጥቶታል። ይህ ሰው ተመሳሳይ አመለካከት፥ ዋጋ (ዋጋ ያለው ነገር)፥ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች የተከበበ ነው። መሆን የሚፈልገውን መሆኑ እና መሥራት የሚፈልገውን መሥራቱ ‹ትክክለኛ› እንደሆነ እርግጠኛ ይሆናል። ከዚህ የተነሣ ግለሰቡ ራሱን ከቡድኑ ጋር አንድ አድርጎ ይመለከታል። የአንድን ቡድን ‹ክብር› ወይም ሕልውና ብትነካ እያንዳንዱን የቡድን አባል በግል አጠቃህ ማለት ነው! ይህ የጠለቀና



መሠረታዊ የሆነ የሰው የመብት ዋስትናና የመሆን ነፃነት በቡድኑ አባላት መሐል የታማኝነትን መተሳሰር ይፈጥራል።»

«በመሠረቱ ፍጹም የበላይ የሆኑ ነገሮች የመኖርን ነፃነት የሚሰጡት በአንዳንድ ቅድመ-ሁኔታዎች ብቻ ነው። ሰው እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፤ በተወሰኑ ሕግጋት መሠረት መኖር አለበት፤ ተቀባይነትን ለማግኘት በሚያስፈልጉ መመዘኛዎችና ለተወሰኑ ዘይቤዎች ራሱን ማስገዛት አለበት። እንደገና ማኅበራዊ የሆነው ቡድን እንደ ምሳሌ ሊያገለግል ይችላል»።

«በሌላ በኩል ደግሞ ቡድኑ ለመኖር ሕልውናው በአባላቶቹ ታማኝነት ላይ ይደገፋል። እውቅናን፥ ደረጃን፥ መቀባበልንና መወዳጀትን የሚሰጠው በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ ነው። የእግር ኳስ ጨዋታ ቡድን ውስጥ መግባት ብትፈልግ፥ የጨዋታውን ሕግ ማወቅና መቀበል አለብህ። በማንኛውም ቡድን ውስጥ ተቀባይነትን ማግኘት በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው። እንግዲህ ይህ ነገር ቡድኖች ‹የቆሙት› ከራሳቸው በሚበልጥ ነገር እንደሆነ ያመለክተናል። ምቹና ፍጹም የሆነውን ነገር፥ ዋጋን ስለ አንድ ነገር ማለትም ከፍተኛ ደረጃን ስለያዘው ነገር ያላቸውን መረዳትና ግንዛቤ የሚወክሉ ናቸው። ቡድኑ ከፈረሰ የቡድኑ ገዢ የሆነው ፍጹም ነገር ኃይሉን ያጣል። ስለዚህ ቡድኑ ለሚገዛለት ከፍተኛ ደረጃ ለያዘው ነገር ስም ሕገወጥ የሆነውን ባሕርይ በንቀት፥ በማንቋሸሽ፥ በማስቸገርና በማስጨነቅ ወይም በማግለል ይቀጣዋል። ቡድኑ ምናልባት የሰጠውን የመኖር መብት ይወስድበታል፤ ወይም በጥያቄ ምልክት ያስቀምጠዋል። በኅብረተሰቡ ዘንድ የተጠላ ወይም የተወገዘ መሆን ደግሞ ‹ከመንፈሳዊ ሞት› ጋር በእኩልነት ደረጃ የሚወዳደር ነው። ይህ ሁሉ ‹ማኅበራዊ ቁጥጥር› ብለን የምንጠራው ነው።»

እያንዳንዱ ሙስሊም ከሌላው ጋር የመወዳጀት ጠንካራ ስሜት አለው። እርሱ ወይም እርሷ የኡማው ማለትም የእስልምናው ማኅበር ክፍል ናቸው። ይህ ማኅበር ደግሞ የሚሰጠው ራሳቸውን ለሠጡት የመወዳጀትን ነገር ብቻ ሳይሆን አባላቱን መከታተልም ጭምር ነው። በአብዛኛው የእስልምና ኅብረተሰብ መሐል ኃጢአትን እንኳ ሳይቀር ቢፈጽም የእስልምናን ተግባራት የማያደርገውን ሰው ይቀበሉታል፤ ምንም አይሉትም። ነገር ግን አንድ ሙስሊም ክርስቲያን ሲሆን በጭራሽ አይቀበሉትም።

«... ከእምነት ቢያፈገፍጉም ያዙዋቸው፤ ግርኩዋቸው። ባገኛችሁበትም ስፍራ ግደሉዋቸው» (ሱረቱ 4፡89)።

በሐዲስና በታሪካዊ ጽሑፎች ላይ አስከፊ ሆኖ የተገለጠው የዚህን ነገር እውነተኛነት የሚያስረዱ እጅግ በጣም ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ዛሬም እንኳ ይህ ነገር እውነት ነው። ምንም እንኳ ‹ግድያ› በአብዛኛው የሙስሊም ኅብረተሰብ ላይደረግ ቢችልም፥ ሙሉ በሙሉ ከኅብረተሰቡ የመገለል፥ ‹ከሐዲ› ተብሎ ከእስልምና፥ ከቤተሰብና ከጓደኞች የመለየቱ ፍርሃት ዛሬም እውን ሆኖ የሚታይ ነው።

«ማኅበራዊ ቁጥጥር የሚባለው ነገር ሁሉም ቡድኖች በውስጣቸው ከሞላ ጎደል አንድ ዓይነት ናቸው ወደሚለው እውነታ ይመራናል። አባላቱ እርስ በርሳቸው ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ያስባሉ፤ ነገራቸውን ይገልጣሉ፤ እንዲሁም ይዛመዳሉ። ከውጪ ካሉት ጋር የተለዩ ናቸው። ሁሉም ቡድኖች የየራሳቸውን የመግቢያ ቅድመ ሁኔታ የያዙ ክልሎች አሏቸው። ሁልጊዜ ደግሞ በውጪ ያሉ፥ ‹የውጪ ቡድን› ተብለው የሚጠሩ አሉ። በነዚህ መሐል ደግሞ በቡድኑ ያሉትን በውስጥ፥ በውጪ ያሉትን ባሉበት ለመጠበቅ ግድግዳ አለ።»

ስለ ‹ውጪ ቡድኖች› ሲጽፍ እንዲህ ብለዋል፡-

«በቡድኑ ላይ ችግር የሚያመጡት ከኅብረቱ ውጭ ያሉቱ ሳይሆን የቆሙለት ዓላማ ነው። ምክንያቱም የትለአየ ግንዛቤ የኑሮ ዘይቤና እምነት አላቸውና። የሚወክሉትና የሚገዙለትም እውነታቸው እንዲሁ የተለዩ ነው። እንዲህ ያለ ሌላ ቡድን ሌላ የተለየ ፍጹም እውነት ይዞ መነሣቱ የማይገሰስ ሥልጣን የነበረውን የፊተኛንው ‹ፍጹም እውነትና› የቡድኑንም አባላት ሕልውና የሚፈታተን ይሆናል። አንድ ጊዜም ተግዳሮት ከገተመው በኋላ በኅብረቱ ላይ የመሠልጠኑ ነገር በእያንዳንዱ አባል ልብ ውስት አብይ ጥያቄ ሆኖ ይነሣል። ለዚህም ነው በኅብረቱ ውስጥ የታቀፉት ባልታቀፉት ላይ ባላጋራ ሆነው የሚነሱበት ምክንያት። በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ኅብረት ውጭ ካሉ ሌሎች ኅብረቶች ሁሉ ራሱን ያገላል። ከውጪኞች ጋር የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ሁሉ ማዕቀብና ቁጥጥር ያለበት ነው። ከውጪኞች የተገኘ መረጃ ሁሉ በጥልቀት ይመረመራል ይጣራል። በሁለተኛ ደረጃ በውጭ ያለው ቡድንና የሚወክለው/የሚገዛበት እውነት ሆን ተብሎ ይንቋሸሻል። የውጪኞቹ ማህበራዊ እሴቶችና የኑሮ ዘይቤዎች ሁሉ ርካሽና ሥነ-ምግባር የጎደላቸው ተደርገው ይቆጠራሉ። የኅብረቱ አባሎችም የማጣጣያ ቅጥያ ሰም (ለምሣሌ አይሁዳዊ፥ ኮሚኒስት-አፍሪካ ወዘተ) ይለጠፍባቸዋል። ያለስማቸው ስም ይሰጡአቸዋል። በአንድ ኅብረት ውስጥ ያሉ አባላት የውጪኞችን ዓላማና ቡድናቸውን በጥልቀት እንዲረዱ አይፈቀድላቸውም። ምክንያቱም ቡድናዊ ለሆነው ዓላማ ታማኝነትን ሊያዛባ ይችላልና።»



ንግዲህ እኛ ልናደርገው የምንፈልገው ነገር ይህንን ሲሆን እስልምናም በኛ ላይ ገድረግ የሚፈልገው ነገር ይህ ነው።

ኑላችንም ይህንን ነገር ተገንዝበናል፡-

«የቡድኑ አባላት ራሳቸውን ከቡድኑና ከርዕዮተ ዓለሙ ጋር አንድ አድርገው ከተመለከቱ፥ በርዕዮተ ዓለማቸው ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ሁሉ በራሳቸው ላይ እንደደረሰ አድርገው ይቆጥራሉ። ስለዚህ ተከላካይ ይሆናሉ፤ ከባሰባቸውም አጥቂ ይሆናሉ። ግብታዊ የሆነ ግንፍልነት ከተከተለ የሚያሳየው ነገር ግላዊ የሆነው መረዳታቸውንና በራስ መተማመናቸውን የመሠረቱበት መሠረት መነካቱን ነው።»

«ቡድኑ የራሱን ግቢ እንደነበር ንጹሕ አድርጎ ጠርጎ ቆሻሻውን በሙሉ ወደ ጎረቤቱ ግቢ በአጥሩ ላይ ይወረውራል እንደ ማለት ነው። ይህም ጥፋትን በሌላው ላይ ማላከክ ብለን እንጠራዋለን። ቡድኑ የሚመለከተው የራሱን ሐሳብ የሚደግፍለትን የእውነት ክፍል ብቻ ነው። ይህን እየመረጡ ማወቅ ወይም ከእውነት መሐል እየመረጡ መቀበል ብለን እንጠራዋለን። ዓለምን ሊረዳው የሚፈልገው ለራሱ በጣም ጠቃሚና ትርፍ በሚያስገኝለት መንገድ ብቻ ነው። ይህን አድላዊነት ወይም ወደሚፈልጉት ማዘንበል ብለን እንጠራዋለን። ቡድኑ አመለካከቱን እውነት ነው ብሎ ለማሳመን ግማሽ እውነትን የያዘ ብልጣ ብልጥ የመከራከሪያ መዋቅሮችንና ከእውነት የተጣመመ ተጠየቅ (ሎጂክን) ይጠቀማል»።

በእስልምናና በክርስትና መሐል በሚደረግ ክርክር ላይ የተሰማሩ ሁሉ ከላይ የተገለጹ ዓረፍተ ነገሮች እውነት መሆናቸውን እየጎረበጣቸው ያስተውሉታል። ክርስቲያኖችም ጭምር ከዚህ ነፃ ናቸው ማለት አንችልም። ምንም እንኳ ስሜታዊ በሆነ ምላሽ የኛን ፍጹም እውነት ብለን የያዝነው ነገር በሚያስቆጣ መንገድ ሲጠቃ መመልከቱ አስቸጋሪ መሆኑን ብንረዳም፥ በክርስትናና በእስልምና መሐል ባሉ ክርክሮች ይህ አብዛኛውን ጊዜ ሙስሊሞች የሚያደርጉት ነው፤ ራሳችንን በመግዛት ለክርስቶስ ሥራ አጥፊ የሆነውን፥ መጽሐፍ ቅዱስም የማይፈልገውን የበቀል እርምጃ ከመውሰድ መቆጠብ አለብን።

ማንኛችንም ብንሆን እየመረጡ ከመቀበል ሌላ አማራጭ ዕድል የለምን። መረጃዎችን በመሰብሰብ ወይም በመቀበል ደረጃ አቋም መያዝ አለብን። ይህን ከፍርሃት ውጭ ማድረግ፥ ሆን ብሎ መሸነፍ ማለት ነው። ነገር ግን እውነትን ያዘለና ምክንያታዊ የሆነ የመከራከሪያ ነጥብ ከኛ ወገን በእርግጥ ካለ፥ መፍራት አይገባንም። ይህ ለራሳችን ሳይሆን ለእግዚአብሔር ነው!

**እኛ መስጋት ያለብን የሙስሊሞችን ጆሮና ዓይን እንዳንዘጋ ብቻ መሆን አለበት።**

አሁን እንዳየነው የመወዳጀትና ተቀባይነት የማግኘቱ ስሜት ለሰው በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ኑርንበርገር በግሩም ሁኔታ እንዲህ ሲሉ አስቀምጠውታል:-

> «የመኖር መብት ከራሱ ከመኖር የበለጠ መሠረታዊ ነገር መሆኑን መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው። ሰው አንድ ጊዜ መሆን ያለበትን መሆኑን፥ መሥራት ያለበትን እየሠራ መሆኑን፥ ፍጹም-ባለ እውነት ብሎ በሚገምተው ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን፥ ለእውነተኛው ሕልውናው እውነት መሆኑን፥ በነገሮች ላይ እርግጠኝነትን ማግኘቱን ወይም የሆነውን ነገር እንበለው እርግጠኛ ከሆነ ማኅበራዊ፥ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጎትን፥ ያለውን ነገር ሁሉና ዕድሉን፥ ጓደኞቹንና ቤተሰቡን፥ የራሱን ሕይወት እንኳ ሳይቀር መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ ፈቃደኛ ነው፤ ይችላልም።»

ይህን ስናነብ ራሳችንን ማየት ችለናል ወይስ ሙስሊሞችን ብቻ ነው የተመለከትነው? የኛን ዋጋ፥ ሕጋችን ወይም ዘይቤያችን ምን ወይም ማን እንደሚወስነው በታማኝነት ራሳችንን መጠየቅ አለብን። ምንም እንኳ ነገራችንን የሚወስነው መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም፥ ማነው መጽሐፍ ቅዱስን የሚተረጉምልን? እዚህ ላይ የአተረጓጐም ዘዴ ጥያቄ እንደገና ይነሳል። ከቡድን ጋር መያያዙ ወይም በሌላ ሰው መደንገጉ በግልጽ ለሚታይ መመዘኛ ወይም የአኗኗር ደረጃ ራሳችንን መስጠት ይገባናልን? ነገር ግን ምናልባት በግልጽ በጊዜ ወይም በቦታ የተወሰነና ዓለም አቀፋዊ ያልሆነ ግብረገብ ወይም ሥነ-ምግባር ሊኖር ስለሚችል፥ የእግዚአብሔር ቃል እስካልተቃረኑ ድረስ ማጤን ያስፈልጋል።

በግልጽ እንደሚታወቀው የእስልምናው ኡማ የእነዚህን ጥቅሶች ገለጻ የያዘ ቡድን ነው። ይህን የምናደርገው በግንዛቤና ወንጌልን በማሰራጨት ላይ ያለውን ውጤት ለማጤን ነው።

> ይህ ሁሉ እንደገና ወደ ግጭት ያመራናል፤ ምክንያቱም ወንጌልን ማሰራጨት ለሙስሊሙ ወይም በእስልምና ዘንድ ከፍተኛ ደረጃቸውን ለያዘው ነገር



> የሚገዳደር ሆኖ ስለሚቀርብ ነው። ለምንድነው ወንጌል የምንሰብከው? ምክንያቱም ለሙስሊሞች ፍጹም እውነት ሌላ አማራጭ ለማቅረብ ነው!

ይህን ነጥብ ለማጠናከር፥ ፕሮፌሰር ኑርንበርገር በመቀጠል እንዲህ ብለዋል:-

> «ፍጹም የበላይነት ባለው ነገር ቁጥጥር ሥር የሆነ ሰው በተወሰነ መንገድ ይሠራል፤ በተወሰነ መንገድ ይከራከራል፤ አንዳንድ ነገሮችን ለማግኘት ጥረት ያደርጋል። ከፍተኛ ደረጃ የያዘውን ነገር ስትገዳደረው ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ይታወካል፤ ፊቱ ይጠቁራል፤ ምናልባትም ስሜታዊ፥ ቁጡ ወይም ወግ አጥባቂ ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው በስሜቱ ከተነዳና ግልብነት የሚያበዛ ከሆነ ያ የሚገዛውና የበላይ የሆነበት ነገር ለመነካቱ ደንበኛ ምልክት ነው።»

እንግዲህ ማነው ሃይማኖታዊ ወግ አጥባቂ? ወግ አጥባቂ የሆነው ሰው የተከፈተ አፍና የተዘጋ አዕምሮ ያለው ሰው ነው ይባላል። በጣም ጠቃሚ የሆነው ነገር የሚፈጸመው ተቀባይነት ማግኘት ስሜትና በቡድኑ ነገሮችን በጥልቀት በመመልከት ላይ ብቻ ሳይሆን፥ ከዚህ ጋር አብሮ ከሚሄደው መረዳትና ግንዛቤ ጭምር ነው።

> «ሰውየው ሕልውናውን፥ ወይም እርሱ የሆነውን ነገር የመሆን መብቱን የመሠረተበትን ከፍተኛ ደረጃ የያዘውን ነገር በጥሩ ሁኔታ ብታጠቃው፥ በውኃ ውስጥ በመስመጥ ላይ ያለ ሰው እንደሚሆነው ዓይነት ምላሽ ታገኛለህ። ይህን ነገር በአንድ ሙስሊም ላይ፥ አንገተ ደንዳና ኃብታምና ለዘብተኛ የእምነት አቋም ባለው ሰው ላይ በክርስቲያንም እንኳ ቢሆን እስቲ ሞክረው። እነዚህ ሰዎች በርጋታ ዝም ካሉ ያ በውስጣቸው የነገሠው ነገር እስከሚነካ ድረስ አልዘለቅሁም ማለት ነው።»

ይህ እውነት ከሆነና ሁሉም በዚህ መሠረት ከተናገሩ፥ ማንኛውንም በሙስሊሞች ልብ የነገሠውን እውነት የማይገዳደር የወንጌል ስብከት የወንጌል ስብከት ልንለው አንችልም። ነገር ግን ይህ መገዳደር ምናልባት አዝጋሚ ሂደት ሊሆን ይችላል። አንድ ልንረዳው የሚገባ ነገር ቢኖር ሁሉም ሰው ስሜቱን በግልጽ የማያሳይ መሆኑን ነው።

> «እነሱ ትክክል እንደሆኑና እውነትን የሚመለከቱት በተጨባጭ መልኩ እንደሆነ አጥብቀው ያምናሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሌላው ቡድን እውነትን ለራሱ ጥቅም ሲል የሚያጣምም እንደሆነ ያምናሉ። ነገር ግን በዚህ ጊዜ እነሱ ደግሞ የራሳቸውን ስሕተት የማወቅና የማስተካከል ችሎታቸውን ያጣሉ፤ እንዲሁም የራሳቸውን የኃላፊነት ድርሻ መሸከም አይችሉም። ስሕተት የሆነውን ነገር በራሱ ተፅዕኖ ሥር ተመልክቶ በድፍረት መፍትሔ በመስጠት ፋንታ እያንዳንዱ

ቡድን ሌላውን እየነቀፈ አንዱ ቡድን አንድ ነገር እንዲያደርግ በፉክክር ይጠባበቃሉ።»

እንደገና ዓይነተኛ የሆነ የእስልምና ገጽታ ቀርቦልናል።

ይህ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ቢሆንም ቅሉ ጸሐፊው እስልምናን ብቻ ለይቶ ለማውጣት በፍጹም አልፈለገም፤ ምክንያቱም ይህ ጥናት በሥነ-መለኮታዊ ሥነ-ምግባር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው። ታማኝ የሆነ አንባቢ የራሱን አቋም በዚህ መሠረት ይመዝናል። እዚህ ላይ ማንሣት የምፈልገው ነጥብ የአንዱን መነሻ ሐሳቦች ከሌላው ለይተን አንቀበልም ስንል ራሳችን ላለንበት ወገናዊነት ወይም አድላዊነት ሳይኖረን ከሆነ የመጨረሻው ጥቅስ እኛን የሚመለከት ይሆናል። በግልጽ እንደሚታወቀው ብዛት ያላቸው ተግባራዊ ውስንነቶች አሉ፤ ይህም ቢሆን መልእክቱ ግልጽ ነው። ሌሎችን ለክርስቶስ መማረክ ማለት ለሌላ ፅንሰ-ሐሳብና አመለካከት መጋለጥ ነው። ምናልባት ሁሉም ይህን ለማድረግ አይችሉ ይሆናል። ወይም በዚህ የተዘጋጁ አይኖሩም ይሆናል። ነገር ግን እውነትን እንደያዝንና እንደምንከተል የምንናገር ከሆነ፥ ሌላው ወገን የሚለውን ለመስማት መፍራት የለብንም። ይህም ክርስቲያናዊ የሆነውን አቋም አዎንታዊ በሆነ መልኩ ለማቅረብና ለምን እንደምናምንበት ለማብራራት ይረዳል። ይህን ነገር ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ይደግፈዋል:-

«ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ ታውቁ ዘንድ...!» (ቆላ 4:6)።

«ልናገር እንደሚገባኝ ያህል እገልጠው ዘንድ ጸልዩልኝ!» (ቆላ 4:4)።

«በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቃችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ!» (1ኛ ጴጥ. 3:15)።

ይህን ነገር ከልባችን ካልያዝነው ማለትም እርግጠኛ መሠረት ሳይኖረው ካመንበት፥ ወይም የሰማነውን ሁሉ ያለማመዛዘን መቀበል ብቻ ከሆነ፥ ወንጌላውያን ሳንሆን እንደ ሌሎቹ እምነቶች ሁሉ የቅስቀሳ (የፕሮፓጋንዳ) አቀንቃኞች ሆነናል ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ ምክንያታዊነት የሌለን ሃይማኖታዊ ወግ አጥባቂዎች ሆነን እንታያለን።



ፕሮፌሰር ኑርንበርገር በደንብ ያስተዋሉት ነገር አለ:-

« . . . ሕዝብን ቢቻል አደናግሮ አለዚያም አስገድዶ ግብታዊና ስሜታዊ ለሆነ ተግባርና ተቃውሞ ማነሳሳት ይቻላል። የሕዝብ ግርግርና ዓመፅ ምናልባት ከዚህ ሊመነጭ ይችላል»።

«ርዕዮተ ዓለም በተመረጠና ወደ አንድ ወገን ባደላ መንገድ እውነትን በመገንዘብ ላይ የተመሠረተ ነገር ነው፤ ለራሱ ጥቅም የሚሆን የመከራከሪያ መዋቅር ለመገንባት ሲል ምክንያታዊ ዘዴዎች ይጠቀማል። ከርዕዮተ ዓለም ጀርባ ያለው ትክክለኛ ይዘት የግል ምኞትና ፍላጎት ነው፤ ስለዚህ ይህ ታማኝነት የጎደለውን ነገር የያዘ ነው ማለት ነው። ነገር ግን ይህ ነገር ሁሉ ሆን ተብሎ የሚደረግ ሳይሆን ባለማወቅ የሚሠራ ሊሆን ይችላል። በእርግጥ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው በራሱ ታማኝነት የሚያምን ከሆነ ነገሩን በከፊል በማወቅ ወይም በከፊል ሆን ብሎ ወደ መሥራት ሊገፋፋው ይችላል»።

«የጨለማውን ዘመን» እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ ነገር የሠሩትን የመስቀል ዘማቾችን (ክሩሴዶችን) ካላሰብን በስተቀር የክርስቲያኑን ቡድን እዚህ ላይ ለመመልከት ያስቸግራል።

አንድ ሰው ወይም በቡድን የተሰበሰቡ ሰዎች የራሳቸውን ሃይማኖትና የክርስትናን እምነት ትምህርቶች በጥልቀትና በእውቀት በመመርመር በማይችሉት ውስብስብና በሆነው የስልምና መዋቅር ውስጥ ገብተው ይታያሉ፤ ነገር ግን እነዚህ ዳር ዳሩ ላይ ወይም ጠርዙ ላይ የቆሙት በፍጹም አይደሉም። ከዚህ ዓይነት ሁኔታ እንኳ የወጡ ሰዎችን እናውቃለን። ፕሮፌሰር ኑርንበርገር በጥናታቸው ከዚህ ነገር በስተጀርባ ሆኖ የሚገፋፋውን ኃይል ገልሸችውታል። እኛም ይህን ነገር በጥንቃቄ ማጥናት አለብን:-

«እኛ ባለንበት የኅብረተሰብ ክፍል አማካኝነት የመኖር መብታችን ቢረጋገጥልንም እንኳ ያ የመጨረሻው ቃል ሊሆን አይችልም።» አንድ ጊዜ አንድ ሰው በጣም ልዩ የሆነ ከፍተኛ ሐሳብ ወይም መረዳት ላይ ከደረሰ፥ ጉዳዩ ካለበት ቡድን ጋር የሚያጋጨው ቢሆንም እንኳ የደረሰበትን ሐሳብ ለማገልገል ፈቃደኛ ነው። ሕይወቱ በአንድ ከፍተኛ ደረጃን በያዘ ነገር ሥር እየሰደደ በሄደ ቁጥር ዕውቅናንና ተቀባይነትን ለማግኘት በአካባቢው ሕብረተሰብ ላይ ጥገኛ መሆኑ እየቀነሰ ይሄዳል»።

«አንድ ሰው እንዲለወጥ ካስፈለገ ሌላ አማራጭ የሆነ ከፍተኛ ነገር ሊቀርብለት ያስፈልጋል። ይህ ብቸኛው መንገድ ነው። ሰው ለሕይወቱ መሠረት የሚሆን ነገር ካላገኘ በስተቀር ይህን ሊያደርግ አይችልም። አንተም ሰውየው የተሻለ ዋጋ ያለውና

የማይነቃነቅ መሠረት የሆነ አግራጭ ማግኘቱን ሳይገነዘብ በፊት እርምጃ እንዲወስድ ልትጠብቅበት አትችልም።»

(ሁሉም ትኩረት የተሰጠባቸው ነገሮች የኛው ናቸው)።

ይህ ግጭት የማይወገድበት ከፍጥጫ የማያመልጡበት ጉዳይ ቢሆንም፥ ስሜታዊ ባልሆነ፥ ርኅራኄ ባለውና መንፈሳዊ በሆነ መንገድ ወንጌል በሙሉ ኃይሉ እየቀረበ ነው።

## «አይነኬዎች»

### አላህ፥ ቁርዓን እና መሐመድ

እነዚህ በከፍተኛ ክብር የተቀመጡ ናቸው። ለሙስሊሞች ከፍተኛውን ደረጃ የያዙ ባለሥልጣኖች ናቸው። ሊታመንባቸውና ሊታዘዙአቸው የሚገቡ ናቸው።

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ቁርዓንን በቃል መጠናት ያለበት (በዐረብኛ) ነገር አድርገው ሲወስዱት፥ በጣም ጥቂቶች ግን ይዘቱንም ማጥናት እንዳለባቸው ተረድተዋል። ምን እንደሚያምኑና እንዴት እንደሚያምኑ በሌላው ይነገራቸዋል። ሙስሊሞች ስለ እስልምና አንድ ዓይነት የሆነ እውቀትና መረዳት ያላቸው ይመስላል፤ ነገር ግን አብዛኞቹ በአንዳንድ ትምህርቶች ላይ (ለምሳሌ ስለፍጻሜ፥ አስቀድሞ ስለ ተወሰነ ዕጣ ፈንታ፥ ስለ ትክክለኛው የጥንት እስልምና ታሪክ፥ ስለ ቁርዓን አሰባሰብና እንደገና ተሻሽሎ መጻፍ ወዘተ) ምንም እውቀት የላቸውም።

ምናልባት ይህንን አንድ ገጠመኝ ሊያብራራው ይችላል፡-

«ሙስሊሞች እኛ እንደምናስበው እንደማያስቡ ተገንዝቤአለሁ። ይህንን ወጣ አጥባቂ ሙስሊም ጥያቄ መጠየቅ ጀመርኩ። ‹እግዚአብሔር የመሐመድን ኃጢአት ይቅር ብሎታል?› አልኩት። ሰውዬውም ጮክ ብሎና በአንክሮ ‹አዎና!› ብሎ መለሰ። ከዚያም ‹መሐመድ ኃጢአት ሠርቶ ነበር?› ብዬ ጠየቅሁት። ጮክ ባለ ድምፅ ‹በፍጹም!› ብሎ መለሰልኝ። እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች ሦስት ጊዜ ጠየቅሁት፤ እርሱም ሦስት ጊዜ ያንኑ መልስ መለሰልኝ። ‹አዎ፥ እግዚአብሔር የመሐመድን ኃጢአት ይቅር ብሎታል!› ‹አይ፥ መሐመድ በጭራሽ ኃጢአት ሰርቶ አያውቅም!›። ለዚህ ወጣት ሙስሊም መሐመድ ኃጢአት ሠርቶ አያውቅም፤ ሆኖም እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር ብሎታል የሚለው ሐሳብ ተስማሚ ትምህርት ነው።



አንድ በአሜሪካ ለአሥር ዓመታት ቆይቶ ወደ ኤደን የመጣ ሱማሌያዊ የሱማሊኛን ቋንቋ ሳጠና ይረዳኝ ነበር። ይህን ሰውዬ እስካገኘሁበት ጊዜ ድረስ እንዲህ ዓይነት ትምህርት በፍጹም አይገባኝም ነበር። ይህንን ገጠመኜን ገለጽኩለትና እንዴት እንደምረዳው ጠየቅሁት። ይህን ትምህርት ለመረዳት ለእርሱ ቀላል ነበርና። እንዲህ በማለት ገለጸልኝ፡- ‹መሐመድ በጭራሽ ኃጢአት የለበትም ለማለት ያስቸግራል›። እኔም ‹አዎን› አልኩት። ‹መልካም› ከዚያም እንዲህ አለኝ፡- ‹እግዚአብሔር የመሐመድን ኃጢአት ይቅር ብሎታል ማለትስ አይመችም?›። እኔም ‹አዎን› አልኩት። እርሱም ‹መልካም፥ እንግዲህ ነገሩን ለመግለጽ መንገዱ ይኸው ነው› አለኝ። እንግዲህ በአንፃሩ ለመሐመድ «ምቹ» የሆነ ነገር ሁሉ ለሙስሊሞች አዕምሮ ትክክል ስለሆነ ይታመንበታል ማለት ነው!»

(«በሙስሊሞች መሐል በግል ነፍሳትን የመማረክ ገጠመኝ» በኤች ዋረን ሞድሪኮር)።

ቁርዓንንና የመሐመድን ሕይወት በዚህ መልክ መተርጐሙ ለሙስሊሞች ትክክለኛ ነገር ነው። ይህንን ነገር አምባገነን የሆነ አመራርና በዚያ ላይ የተመሠረተ ትምህርት ባለበት በሁሉም ቡድን ውስጥ እናገኘዋለን።

ይህ ነገር «ታ-አቡዲ» የተባለው ፅንሰ ሐሳብ ባሕርይ ነው። አላህ፥ መገለጡ፥ ሕግጋቱና ፅንሰ ሐሳቡ «ያለምንም ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘት አለባቸው»። ይህ ሁሉ «ጠይቀን ልንደርስበት የማይቻል ጥበብ ነው። የተመሠረተውም በምንም ዓይነት ሕግ በማይያዘው በአላህ ፈቃድ ላይ ነው»።

(«የእስልምና መዝገበ ቃላት» በኤች.ኤ.አር.ጊብ እና በጂ.ኤች. ክሬይመርስ ገጽ 525።)

በዚህ መነሻ ሐሳብ በመታሠራቸው የእስልምና ሥነ-መለኮታውያን ቁርዓንና ሐዲስን በትንተና በደንብ እንዳይጠኑ ዘወትር ይቃወማሉ። እነዚህ ነገሮች ሊታመንባቸውና ሊታዘዝአቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው፤ ጠንከር ያለ ጥያቄ ሊቀርብባቸው አይገባም!

ይህ ነገር ምናልባት በ «ምዕራቡ» ዓለም ላይ ለምን ከፍተኛ ተቃውሞ እንዳላቸው ይገልጽ ይሆናል። ውጫዊ የሆነው ምክንያታቸው የሥነ-ምግባርና የግብረገብ ብልሹነት፥ ቁስ አካላዊነት እና ዓለማዊነት ስላላቸው ነው ቢሉም እኔ ግን የእስልምና ምንጮችን ጥልቀት ባለውና ታሪካዊ በሆነ መልኩ ይጥልብናል የሚለው ነገር

እንዳይመጣ ፍርሃት ይዟቸው ይመስለኛል። ይህ ደግሞ ለእስልምና እጅግ አደገኛ ነገር ነው።

ሙስሊሞች በጣም አስቂኝ የሆነውን የለዘብተኞችንና የዘመናውያን «ክርስቲያን ምሁራንን» ንግግሮች በመንቀፍ መጽሐፍ ቅዱስን በጥያቄ ላይ ለመጣል ሲፈልጉና ሲያደርጉ ቢታይም፥ የራሳቸውን ቁርዓንና ባህላዊ ጽሑፎቻቸውን እውነተኛ በሆነ ምሁራዊ ግምገማ እንዳይታይ እምቢ ማለታቸው እንቆቅልሽ ከመሆኑም በላይ እርስ በርሱ የሚያጋጭ ሐሳብ ነው።

**ሙስሊሞች ቁርዓንን ይቀራሉ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ያጠናሉ።**

## የኃይል መመሪያ

አላህ ፍጹምና ሉአላዊ የሆነው ገዢ ተደርጎ ተወስዷል። የአላህ ዋና ባሕሪም ኃያልነት ነው። ምናልባት ከዚህ የተነሣ ይሆናል እስልምና ለአላህ ለመገዛት የቆመው። ይህንን ነገር ለማስወገድ አንድ ሙስሊም ነገሩን በጥንቃቄ የሚያጤንበት ምንም ዓይነት መንገድ የለውም። ነገር ግን ከዚህ ነገር የተነሣ ሰውዬው ራሱን ከአሸናፊው ወገን አድርጎ ይመድበዋል!

ሙስሊሞች ከመጀመሪያ ጀምሮ ከዚህ የኃይል ክስተት ጋር ተለማምደዋል። ምንም እንኳ ሙስሊሞች ይህን ለመካድ ቢሞክሩም፥ ቅዱስ ጦርነት ቀድሞም ሆነ አሁን የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ምልክት ነው። ሙስሊማዊት ዐረቢያ የተመሠረተችው በጉልበት ነበር። ከመሐመድ ሞት በኋላ እስልምናን ለማስፋፋት በወታደራዊ ኃይል መሆኑን ግልጽ ነው።

«አላሁ አክበር» - አላህ ታላቅ ነው! በሸሪያ (በሙስሊማዊ ሕግ) አማካይነት በሁሉም ስፍራ አላህ መግዛት አለበት። ይህ ሕግ በሁሉም ሀገሮች ላይ ቀስ በቀስ መጫን አለበት። ለዚህም እስልምና ዓለምን በሁለት ክልሎች ከፍሎአታል፡-

## ዳሩ›ል - ሙስሊም እና ዳሩ›ል - ሐርብ

## የእልምና ክልል እና የጦርነት ክልል

ዓላማው የመነጨው የእስልምና ሥነ-መለኮት ምሁራን ‹አላህ የሚገዛት መንግሥት› ብለው ከሰየሙት ጽንሰ ሀሳብ ነው። አላህ ከፍተኛው ገዢ ነው፤ ስለዚህ ዓለም በሙሉ ለእርሱ ሊገዛለት ይገባል። ይህንን በግድ ለማስፈጸም የሸሪያ ሕግ በሁሉም ሀገሮች መመሥረት አለበት። ሸሪያ ያልተመሠረተበትና በሥራ ላይ



ያልዋለበት ቦታ ሁሉ አሁንም የጦርነት ክልል ነው። ይህ ክልል አሁንም ቢሆን በጦርነት ወረራ ተደርጎበት ለአላህ መገዛት አለበት።

እያንዳንዱ ለሙስሊሞች የሚመሰክር ክርስቲያን ይህንን ቅድመ ሁኔታ ማወቅ አለበት፤ ምክንያቱም መንፈሳዊ የሆነው ውይይት (ንግግር) በዚህ ዓይነት ከጀርባው ባለ አስተሳሰብ ተፅዕኖ ሊደረግበት እንዲያውም ከነጭራሹ ሊወሰን ይችላል።

**ፊት ለፊት መጋፈጥን ለማስወገድ ክርስቲያኖች ክርክርን ለስለስ አድርገው ካቀረቡ ወይም ትሕትናን ካበዙ ይህ ነገር በእርግጥ የድካም ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል።**

## የሙስሊሞች ግፊት

ይህ ሁሉ የሚገለጸው እስልምና ለውጊያ የተዘጋጀና አብዛኛውን ጊዜ ጭፍን፥ በጉልበት የሚጠቀም፥ እንዲሁም የፈላጭ ቆራጭነት መንፈስ ያለበት መሆኑን ነው። ይህ ጉዳይ ሙስሊሞች ጥቂት በሆኑበት ሀገሮች እንኳ ሳይቀር የሚታይ ነገር ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በፖለቲካዊ ጉዳይ ወይም በትምህርቶቻቸው የተለያዩ ሐሳብ ያላቸውን፥ እርስ በርሳቸው የሚሰዳደቡትን የእስልምና ቡድኖችም መመልከት አለብን።

ነገር ግን ሙስሊሞች ውጊያ የሚያካሂዱት በጦር ሜዳ ብቻ አይደለም። አንድ ወጥነትን ለመጠበቅ ቢሞጉም ቅሉ በመሐላቸው ከፍተኛ መከፋፈል አለ። ይህ ጉዳይ ከእዚህ በታች በተገለበጠው የበራሪ ጽሑፍ ማስታወሻ በደንብ ይብራራል። የቋንቋው አጠቃቀም ራሱ እርስ በርስ መከባበር በፍጹም እንደሌላቸው ያሳያል።

## ታጅዲድ አል - ሙስሊም

## (ለእስልምና ተሐድሶ መዋሃድ)

## ለሙስሊሞች ሁሉ ክፍት የሆነ ጥሪ

«ለብዙ ዓመታት ዛሬም ራሳቸውን የሾሙትና ዲሞክራሲያዊ ያልሆኑት ሙስሊም አሃይማኖት መሪዎች (ኡ-ላማ) «የእምነት ሊቀካህናት» ተብሎ እንደሚጠራው ዓይነት ራሳቸውን ሰይመዋል። ነገር ግን ይህ ደረጃ ከቅዱስ ቁርዓን መሠረታዊ ትምህርቶች ጋር ሙሉ በሙሉ የማይስማማ ነው። በእርግጥ በእስልምና ምንም ዓይነት የክህነትም ሆነ የሃይማኖት መሪዎች ክፍል የለም።»

«ነገር ግን ምክንያታቸው የተለያየ ቢሆንም አያሌ፥ በከፊል የተማሩ ሙስሊሞች በነዚህ ዓመታት ውስጥ በሐሰት ራሳቸውን «የተማሩና ምርጦች» አድርገው ሲቆጥሩ

ቆይተዋል። ይህ ከፊሉ መሐይም የሆነው ቡድን የሙስሊሞችን መንፈሳዊ ሕይወት እንደፈለገ ሲነዳው ቆይቷል።

«ሥነ-መለኮታዊ ስሕተታቸውንም ወይም ሥነ-ምግባር ያለልክ እንደሚያበዙ አውቆ የሚታወግቸው ወይም የሚቆጣጠራቸው ትክክለኛ ኃይል ባለመኖሩ የሙስሊሙ ሃይማኖታዊ የሥልጣን ተዋረድ መዋቅር (በተለይም የእስልምና የሕግ ምክር ቤት) ዛሬ ራሱ ለራሱ ሕግ ሆኗል። ይኸው አልበቃ ብሎ በግልም ሆነ በሕብረት ለሚሠሩት ጥፋትና ዋልጌነት ማንም የሚጠይቃቸው የለም። ይህ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው የሕዝብን አደራና ኃላፊነት ወደጎን መጣል ለነዚህ ‹ኡ-ላማ›ዎች ዋልጌነት መጨመር አስተዋፅኦ አድርጓል»።

«እጅግ ብዙ የሆኑ ሆነ ተብለው የሚደረጉ ጥፋቶች ለምሳሌ ሕገወጥ የሆነ ‹የአስቸኳይ› ፍቺ መፈጸም፥ ዓይን ያወጣ የገንዘብ ዘረፋ፥ ኃጢአትን በተሞላ ሁኔታ የአላህን መስጊድ ወደ ራሳቸው የግል ንብረት መለወጥ፥ በአረመኔያዊ ሁኔታ ፀረ-ልዩ ትምህርት ሆነው ጠንቋዮችን ማደን፥ ጭከና በተሞላ ሁኔታ ቤተሰቦችን መለየት፥ አስቀያሚ በሆነ መልኩ ለነጋዴዎችና ለሌሎች የሰለጠኑ ሰዎች ጉዳቸው እንዳይወጣ ገንዘብ መስጠት፥ አንዳንድ የሚያመልኩ ሰዎችን ቁርዓናዊ ባልሆነ መንገድ ከመስጊዶች ማስወጣት፥ አሳፋሪ በሆነ መንገድ የመስገድ፥ ንብረትን መሸጥ፥ በሚያሳዝን መልኩ በመስጊድ የተዘጋጀውን ምግብ መሸጥ፥ የሚታወሙአቸውን በከባድና አስከፊ ሁኔታ ማስፈራራት፥ እምነትን ሥርዓታዊ ማድረግ፥ ኋላ ቀር የሆኑ ባሕሎችን ችላ ማለት፥ በታላቅ ምሥጢራዊ መንገድ ከጀርባው የሲ.አይ.ኤ. ድጋፍ ያለበት ራቢጣ ለኡላማዎች ጉቦ መስጠትንና ሌሎችም ብዙ እጅግ የሚያስቆጡ ነገሮች በእስልምና ስም መፈጸም እንደ ትክክለኛ ነገር ተወስደዋል።»

«በሚያስቅቀው ድርጊታቸውና ዘበት በሞላበት ሥራቸው ጠባብ አዕምሮ ያላቸው እነዚህ የእስልምና መሪዎች ለግል ጥቅማቸው ሲሉ የእስልምናን የመጀመሪያውን መልእክት አጣመዋል! ጠምዝዘዋል! እንዲሁም አበላሽተውታል። በዚህ ሁኔታ እነዚህ ሰዎች በእስልምና ላይ ከፍተኛ ስድብ፥ ውርደትና ነቀፋ አምጥተውበታል። ዛሬ ሙስሊሞች ሁሉ የሰው መሳቂያ ሆነዋል።»

«እንዲያውም ባይገርማችሁ በሙስሊሙ ኅብረተሰብ መሐል በፍጥነት እየባሰበት የሚሄደው ይህ ሁኔታ ነው።

ዛሬ ታላቅ የሆነ መዘባረቅና የማኅበራዊ ሚዛን መዛባት ደረጃ ላይ ሳይደርስ ፈጣን የማስተካከያ እርምጃ ያስፈልገዋል! ምክንያቱም ጉዳዩ በቀውስ ውስጥ ነው።

«ይህንን ሙስሊማዊ ያልሆነ የውንብድና ድርጊት እያየለ እንዳያድግ ለማገታት ምንም ዓይነት ሕጋዊ የሥልጣን አካል በሌለበት በዚህ ወቅት ሥነ-መለኮታዊ ሥርዓት



አልበኝነትንና ሃይማኖታዊ ፈላጭ ቆራጭነትን ለመፋለምና ለመቆጣጠር አዲሱ አጣሪ ቡድን ሥራውን ጀምሯል። ይህ ልዩና ድፍረት የተሞላው ግብ ታላቁ «ጡጫ» ይሆናል! እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ሁሉ ይደገማል።

## እስልምና በሁሉ ቦታ ገዢ እንዲሆን!

ይህ በእንዲህ እንዳለ አሁንም እስልምናን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማዳረስ በቁርጠኛነትና በቅንጅት ሥራው ቀጥሏል። አፍሪቃና የመካከለኛው ምሥራቅ የመጀመሪያዎቹ ዒላማዎች ናቸው። በእርግጥ አፍሪቃ የመጀመሪያዋ ሙስሊማዊት አህጉር እንድትሆን ስለታቀደ፥ የልማት ሥራዎች ሁሉ ወደዚሁ አቅጣጫ እያመሩ ነው።

በኅዳር 1989 እ.ኤ.አ.፥ በአቡጃ ናይጄሪያ ውስጥ እስልምና በአፍሪቃ የተባለው ጉባኤ ተካሂዶ ነበር። በዚያው ቦታና በዚያው ጊዜ «የእስልምና በአፍሪቃ ድርጅት» (አይ. ኤ.አ) ተመሠረተ። በጋራ መግለጫ ዓላማውና ዕቅዱ ተነደፈ። ከዚህ ቀጥሎ አንዳንድ ከዚያ ላይ የተወሰዱትን እንመልከት (የጋራ መግለጫው ሙሉ ቃል በመጽሐፉ መጨረሻ [ተጨማሪ ገጽ] ላይ ይገኛል።)

ጉባኤው በአህጉሪቱ የሚኖሩ በሸሪያ ሕግ የመታደደር መብታቸውን የተነጠቁት ሙስሊሞች ናፍቆት ምን እንደሆነ ጠቅሶ፥ ይህንኑ ሕግ እንደገና ለመመሥረት በሚደረገው ትግል ሁሉም እንዲገፋበት ያደፋፍራል።

«ሙስሊሞች ... ከወንድሞቻቸው ጋር እንዲተባበሩ ... የአላህን ትዕዛዝ የሚፈጽም ጠንካራና የተባበረ ኡማ (ማኅበረ ምእመናን) እንደገና እንዲመሠርቱ ማድረግ አለብን» በማለት ወስኗል።

ነገሩን የተገነዘበ አንባቢ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ያውቃል:- ሸሪያ የግድ መመሥረት አለበት (እንደገና መመሥረት አይደለም!) ይህም በአህጉሪቱ የሚኖሩ ሙስሊሞች ሁሉ አህጉሪቱን ሙስሊማዊ ለማድረግ እንዲችሉ ነው። ይህ ደግሞ ያለከርከር የአላህን ትዕዛዝ መፈጸምን ያመለክታል።

ይህ ነገር እንዴት በተግባር ሊተረጎም ይችላል? የሚለው ጥያቄም በግልጽ ተመልሷል:-

«በንግድና በሌሎች ሙያዎች በመሠማራት ራሳቸውን ችለው ምርታማ ሊሆኑ የሚችሉ የዳ›ዋህ (ሙስሊም ሚሲዮናውያን) ሠራተኞችን ለማሠልጠን ... ማዕከሎችን ... ማዘጋጀት። ... ይህም የዳ›ዋህን ሥራ በመላው አፍሪቃ

ለመርዳት፥ ለመደገፍና ለማዳረስ ብሎም እስልምናን በአህጉሪቱ በሙሉ ለማሠራጨት ነው»።

ይህ ጉዳይ ተገቢ መሆኑን እኛም ሙሉ በሙሉ እንስማማበታለን። ምንም እንኳ ሁሉም ባይሆኑ አብዛኞቹ የሙስሊም ሀገሮች ክርስትና በምድራቸው ላይ እንዳይስፋፋ ይፈልጋሉ፤ ወይም አጥብቀው ይቃወማሉ። ስለዚ ትክክል ነው የሚሉትን ነገር ክርስቲያኖች እንዳያደርጉት ይከለክላሉ!

ዳሩ ግን የጋራ መግለጫው:- «ለሙስሊሞች በሙሉ፥ ሸሪያን መመሥረትና በሥራ ላይ የማዋል ድጋፍ እንደሚሰት ያረጋግጣል» ድረስ ይቀጥላል። በአንድ ሀገር ውስጥ ሁለት የተለያዩ ሕጎችን መመሥረትና በሥራ ላይ ማዋል የማይመስል ነገር ነው። ስለሆነም ይህ አባባል የሸሪያ ሕግ አሁን ያለውን ሕግ መተካት አለበት ማለት ነው። ከውኃ የቀጠነውን የመቀጫ ሕግ ስንመለከት ምናልባት ከአሁኑ ሕግ ልዩነቱን መመልከት እንችል ይሆናል፤ ነገር ግን ክርስቲያኖች እምነታቸውን (ለሙስሊሞች) መስበክ አይችሉም፤ ወይም የተለወጠው ሰውዬ በሞት ወይም በሌላ ቅጣት ይቀጣል የሚለውን የሸሪያ ሕግ ልንቀበለው አንችልም።

በምንም ዓይነት የሥነ ምግባር መስፈርቶች ያልተያዘ ሕግ «የአባል ሀገሮች ሙስሊሞች ብቻ በብሔራዊና በዓለም አቀፋዊ ደረጃ ስትራቴጂካዊ በሆኑ የሥልጣን ቦታዎች ላይ እንዲቀመጡ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ነው»። ምንም እንኳ በስም የተጠቀሱት ሀገሮች 9 ብቻ ቢሆኑም፥ 24 የሚሆኑ የአፍሪቃ ሀገሮች እንደተወከሉ መረጃ ተገኝቷል። ይህም ሆና በስም ከተጠቀሱት ሀገሮች መሐል ናይጀሪያና ታንዛንያ ሲገኙባቸው። የነዚህ ሀገሮች ዜጎች አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ናቸው። (ነገር ግን ምናልባት ግማሽ ያህል የስም ክርስቲያኖች ይሆናሉ)።

የጋራ መግለጫው በመቀጠል ሲያብራራ እንዲህ ብሏል:- «በአባል ሀገሮች ውስጥ ያሉትን ማንናቸውንም ከእስልምና ውጪ የሆኑትን ሃይማኖቶች (ክርስትናም ይጨመራል) ከነይዞታቸው እና መዋቅራቸው ጭምር መደምሰስና በሁሉም የአባል ሀገሮች የፖለቲካ ሥልጣን ላይ ሙስሊሞች ብቻ መመረጣቸውን ማረጋገጥ አለብን»። ከዚህ በተጨማሪ «ከፍተኛው ግባችን በሚቀጥለው የእስልምና በአፍሪቃ ኮንፍራንስ ጊዜ ከመድረሱ በፊት በሁሉም አባል ሀገሮች ምዕራባዊ ይዘት ያላቸው ማንኛውም የሕግና የፍትሕ መዋቅሮች በሙሉ በሸሪያ መተካት አለባቸው!»

ይህ ምን ዓይነት «ምርጫ» ነው የሚሆነው? በቤተክርስቲያንስ ላይ ምን ዓይነት ውጤት ያመጣል ወይም ሊያመጣ ይችላል? በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጠው ያስፈልጋል።



ማንኛውም ሰው በግልጽ ሊያስተውል እንደሚችለው፥ ዛሬ በብዙ ሀገሮች የዚህ የጋራ መግለጫ አፈጻጸም ሂደት እየተጧጧፈ ነው። ምንድነው ማድረግ ያለብን? እንዴት ነው ለዚህ ጉዳይ ምላሽ የምንሰጠው?

እስልምና ወደፊት በመግፋት ላይ ያለው በአፍሪቃ ብቻ አይደለም። በአውሮፓም በተመሳሳይ መልኩ ቀጥሏል:-

> በ1980/ እ.ኤ.አ./ መጀመሪያ ላይ፥ የእስልምና መሠረት በሊሲስተር የተባለው መረጃ ግልጽ በሆኑት ዓረፍተ ነገሮች ፍላጎቱን እንዲህ በማለት ገልጿል:-
>
> «... ሙስሊማዊው እንቅስቃሴ ዛሬ ያለውን ሕብረተሰብ በቁርዓንና በሱና መሠረት ወደ ሙስሊም ኅብረተሰብ ለውጦ ሙስሊም ለማድረግ የሚደረግ የተቀነባበረ ትግል ነው፤ ይህም በተለይ በማኅበራዊና በፖለቲካዊ ገጽታው ልንደርስበት የሚገባ ከፍተኛው፥ የበላይ፥ የአጠቃላይ ሕይወታችን መመሪያ ነው።»

«... የዚህ ተግባር ይዘት መመሥረት ያለበት የእስልምናው እንቅስቃሴ ከፍተኛውን ግቡን ሊመታ የሚችለው ትግሉ በየአካባቢው ሲቀጥል መሆኑን በመገንዘብ ላይ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም ኅብረተሰቡን ወደ ሙስሊም ኅብረተሰብ የመለወጥ ኃይል ያላቸው በእያንዳንዱ አካባቢ ያሉ ሙስሊሞች ናቸው።»

(ከ «የጊዜው አስተዋይ ሰው» (ዎችማን አፕዴት) ዲሰምበር 1991 የተወሰደ በዶክተር ክሊፎርድ ዴንቶን)

## ሙስሊሞች «በሕግ ሥር» ናቸው

አንድ ሙስሊም በእርግጥ «በሕግ ሥር» ነው። ነገሩን ቢቀበለውም ባይቀበለውም

- ሕጋዊ ወይም የተፈቀደ እንዲሁም
- ሕገወጥ ወይም የተከለከለ፤
- መሠራት ያለባቸውና መሠራት የሌለባቸው፤ በሚሉት ፅንሰ ሐሳቦች የበላይነት እየተገዛ

የሚኖር ነው።

በመጻሕፍቱ መሠረት የሚመራ ሙስሊም ከሆነና ለዘብተኛ ወይም ‹ሱፊ› ካልሆነ እያንዳንዱ የሕይወቱ ጊዜ ለዚህ ግንዛቤ ተገዥ ነው የሚሆነው።

አንድ ሙስሊም የሚኖረው በሕግጋት ነው፤ ማለትም «በሕግ ሥር» ነው (ገላ. 3፡10፤ 5፡3-4፤ ሮሜ 3፡28፤ 10፡4)።

ሕጉን በሚጥስበት ጊዜ በአንዳንድ በጎ ሥራዎች በመሥራት (ምፅዋት መስጠት፥ ተጨማሪ ጸሎት መጸለይ፥ ተጨማሪ ጾም መጾም፥ ቅዱስ ጉዞ በመጓዝ ወይም ሌላ አገልግሎት በመስጠት) ለማካካስ ይሞክራል።

ከዚህ በተረፈ በቁርዓን ውስጥ ብዙ ቦታ በተጠቀሰው፥ ነገር ግን ምንም ዋስትና ባልተሰጠው በአላህ ምኅረት፥ ጸጋና ይቅርታ ይተማመናል። ስለዚህ አንድ ሙስሊም በምንም ዓይነት በአላህ ፊት ያለውን ቦታ በእርግጠኝነት ማወቅ አይችልም።

ሐዲስንና ቁርዓንን ከሞላ ጎደል የሚያውቅ ሙስሊም ሞትንና ፍርድን፥ እንዲሁም በመቃብር ያለውን ቅጣት ይፈራል።

ከዚህ በተጨማሪ የመጨረሻው ፍርድ ስለሚያመጣው ስለዘላለማዊው መድረሻው እርግጠኛ አይደለም።

ነገር ግን በኃጢአቱ ምክንያት በገሃነም ከተቀጣ በኋላ ወደ ገነት እንደሚገባ ተስፋ ያደርጋል።

ከሁሉም በላይ የሚፈራውና ምሕረት የሌለው ኃጢአት ለአላህ ሸሪካ ማበጀት ወይም ክርስቶስን እንደ ‹ሌላ አምላክ› በመቀበል ለአላህ እኩያ ማበጀትን ነው።

በነዚህ ሁሉ፡-

* በቡድን አባልነት ስሜቱ
* ስለ እስልምና፥ ስለ ቁርዓንና ስለ መሐመድ ባለው መረዳቱ
* እስልምናና ከሁሉ የበላይ አድርጎ በመመልከቱ
* ባለው የገሃነምና የመወገዝ ፍርሃቱ
* ፀረ-ክርስትና በሆነው ጥላቻው

አንድ ሙስሊም ምናልባት ከማንኛውም ሰው ይልቅ ለክርስትና መልእክት ተቃዋሚ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም የክርስትናን መልዕክት በተዛባ መልኩ ለመረዳት አዕምሮው የተዘጋጀ ነው።

**መልእክታችን የሚገባና ትርጉም ያለው እንዲሆንለት የተሳሳተውን «የአስተሳሰብ መንገዱን አፍርሰን» ትክክለኛ የሆነውን «የአስተሳሰብ መንገድ» ልናስይዘው ይገባል።**

ይህን ስንል የክርስትናውን መልእክት ከሙስሊሙ የአስተሳሰብ አድማስ ጋ አቀናጅተን ሊገባው በሚችል ግልጽ በሆነ መንገድ እናቀርብለታለን ማለት ነው።



ይህ ነገር ክርስቲያናዊ ፍቅር ነው እንጂ የሚዋዥቅ ስሜት አይደለም፤ እንዲሁም ሰውን ባለበት ሁኔታ በሰብዕናው አክብሮ ለመቀበል ፈቃደኛ መሆንን የሚጠይቅ ነው። ሐሳቡንና ስሜቱን፥ ደስታውንና ፍርሃቱን፥ እምነቱንና አመለካከቱን መረዳት የወንጌልን መልእክት ለእርሱ ትርጉም ባለው መንገድ ለመግለጽና ለመናገር ያስችለናል። ያለበለዚያ ለራሳችን ብቻ እየተናገርን ከሌላው መቆጠብ አለብን።

## ባህልንና አስተዋፅአውን መረዳት

### የባህል ትርጉም

አንድ ሰው አንድ ጊዜ እንዲህ ብሎ ነበር፡-

«እኛ፥ ነገሮችን እንደ ሁኔታችን እንጂ እንደ ሁኔታቸው አንመለከታቸውም!»

የእኛ ምንነት በብዙ ነገሮች ይወሰናል፤ ከእነዚህም ባህል በጣም ወሳኝ ድርሻ ያለው ጉዳይ ነው።

እስቲ ባህል የምንለውን ነገር በጥሩ ሁኔታ እንመልከተው። ባህል «አንድ ኅብረተሰብ በመማር ወይም በልምምድ ሊያገኘው የሚችለው የተወሳሰበ የባሕርይ፥ የአስተሳሰብ የአጠቃላይ ይዘቱ ገፅታ የሚታይበት መዋቅር ነው» በማለት ፖል አይበርት የተባለው የፉለር ሲሚናሪ አንትሮፖሎጂስት ተናግሯል።

«ባህል ሰው ከኅብረተሰብ ወደ ኅብረተሰብ በሚተላለፍ ትምህርትና ልምምድ የሚያገኘው አጠቃላይ ገፅታ ነው፤ ባጭሩ ማኅበራዊ በሆነው ትምህርት የሚወረስ ባሕሪይ ማለት ነው» (ሮበርትሰቶን ምኩልኪን የኮሎምቢያ የመጽሐፍ ቅዱስ ሴሚናሪ አስተዳዳሪ)።

እኛ ልናተኩርበት ለሚገባን ለዋናው ዓላማችን ማለትም ለወንጌል ሥርጭት ባሕልንና ያለውን አስተዋፅኦ መረዳት ማለት፡-

* መልካም ዜና የሆነውን ወንጌል በአንድ በተወሰነ ሁኔታና ባህል ለማስተላለፍ እንዲረዳን እንዲሁም።
* ይህንንም ሥር እንዲሰድና ከባህሉ አንዱ ክፍል ለማድረግ ነው።

በዚህ ላይ እንግዲህ ሥነ-መለኮት፥ አንትሮፖሎጂ (ስነ-ሕዝብ) እንዲሁም ግንኙነቶች በአንድ ላይ ይጣመራሉ። የተዛባ መረዳት እንዳይኖር እስቲ ይህን ነገር

የበለጠ ላብራራው። ስለ እግዚአብሔርና የእግዚአብሔር የሆነ እውቀት መተርጎም ያለበት ወደሌላ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን፥ ወደ ሌላ የሰዎች አስተሳሰብና ልምምድም ጭምር መሆን አለበት።

ይህ ነገር አብዛኛውን ወንጌል የማሠራጨቱን ፅንሰ ሐሳብና መፈክሮችን በተወሰነ መልኩ በመቅረፅ፥ እያንዳንዷን ዝርዝር ጉዳይ በጥልቀት በማየት፥ በዘዴ በመጠቀም፥ ሰው ሊረዳው በሚችለው መንገድ፥ የሌሎችን ሐሳብ ልክ እንደ እነሱ ሆኖ በመረዳትና የሥነ-ቋንቋ እንዲሁም የመረዳት ችሎታንና ነገሮችን የመግለጽ ችግሮችን በሚገባ ማጤንን ይጠይቃል። ዓላማችን የተወሰነ የባህል ስብጥር ላለው አድማጭ በአስተሳሰባቸውና በአኗኗራቸው ሊንፀባረቅ በሚችል ሁኔታ ዘላለማዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን የእውነት ቃል ለማስረዳት፥ ለማስገንዘብና ለማሳወቅ ነው።

የተወሳሰበ ሐሳብን ለማስተላለፍ የምንጠቀምበት ብቸኛ መንገድ ቋንቋ ነው ለማለት እንችላለን። ቋንቋ በመጀመሪያ በተደራጀ ሁኔታ ያደገውና የዳበረው እንደ ዛሬው የባህሎች ግንኙነት በሌለበትና ለረጅም ጊዜ የአንድ ባህል መተሣሠር ባለበት ኅብረተሰብ መሐል ነው። በኋላም በባህሉ ውስጥ ባለው ልምምድ አንፃር ቃላት፥ ሰዋሰው፥ ሐረጎችና ፈሊጦች ተሳክተው ቀርበዋል። የባህል ስብጥር ባለበት ተልእኮ ውስጥ ይህ ጉዳይ ለክርስቲያናዊ ተከእኮ ችግር አያስከትልም።

## ባህል ነክ የግንኙነት ችግሮች

«የወንጌልን መልእክት» ለማጠናቀርና በኡርዱ፥ በግለይ ወይም በሱዳን ቋንቋ ለማስተላለፍ ስንሞክር በመዝገበ ቃላት ላይ ብቻ ጥገኛ ከሆንን፥ ለሚጻፍላቸው ሰዎች ይዘቱ ግልጽ አይሆንላቸውም። ሙያዊ በሆነ መልኩ ለምሳሌ «ነፋስ» (ዊንድ) ብለን የምንጠራው የእንግሊዝኛው ቃል ሰዓቱን ለመሙላት ይጠቀሙበታል፤ የሚነፍስ ነፋስን ሊያመለክት ይችላል፤ ሕፃን «የሚያስወጣውን» ሊያመለክት ይችላል። «ዩኒፎርም» የምንለውም የእንግሊዝኛ ቃል አንድ ዓይነት የሆነ የሚል ትርጉም ሊይዝ ይችላል፤ ወይም የልብስ ዓይነት ወዘተ... ሊሆን ይችላል። የእነዚህ ቃላት ትርጉም የሚወሰነው በአገባባቸውና የሚጠቀሙባቸው ሕዝቦች ባላቸው ልምምድ ላይ ነው። ይህ ጉዳይ የቋንቋ ጥናትን የሚመለከት ነው። መንፈሳዊ ይዘት ያላቸውን ነገሮች ለማስተላለፍ ስንሞክር በጣም ልዩ የሆነ ትርጉም ወይም ይዘት ባላቸው ቃላት ለምሳሌ እንደ፦ «መለወጥ›፥ ‹ደኅንነት›፥ ‹ንስሐ›፥ ‹ጸጋ›፥ ‹ክርስቶስን መቀበል› ያሉትን



ከተጠቀምን የበለጠ ውስብስብ የሆነ ነገር ይፈጠራል። እነዚህ ቃላት በወንጌል አማኞች ብዙ ትርጉም ያላቸው ናቸው። አንድ ካቶሊክ ምናልባት በነዚህ ቃላት ለየት ያለ መረዳት ሊኖረው ይቻል ይሆናል። ለሂንዱ፥ ለሙስሊም ወይም ለቡድሃ እንግዲህ ምን ያህል ርቀት እንዳላቸው መገመት ይቻላል። እንደ ‹የእግዚአብሔር ልጅ›። ‹ሥላሴ› እና ‹ስቅለት› ያሉት ጥቂት የምንጠቀምባቸው ፅንስ-ሐሳቦች ደግሞ አሁንም የበለጠ ውስብስብ ናቸው!

ይህ ቢያንስ ቢያንስ የሰውዬውን የሃይማኖት መረዳት ወይም የሕይወት ፍልስፍና በአጠቃላይ የዕውቀት ደረጃ የማወቅን አስፈላጊነት ያስገነዝባል፤ በተጨማሪም ሃይማኖታዊ የሆነ የቃላት አጠቃቀሞችን ምን ያህል እንደሚረዳቸው መገንዘብ አለብን። የተለያየ ባህል ላላቸው ሰዎች ስንመሰክር ምን ያህል ነገሮችን መረዳት አለብን!

**ነገሮችን በጥልቀትና በብስለት መረዳት የምንችለው ከሰዎች በመማርና በማዳመጥ ብቻ ነው።**

አንዳንድ ግልጽ የሆኑ ጥያቄዎች በዚህ ላይ ይነሣሉ፦

* (ለሙስሊሞች) ወንጌል ማድረሱን ከመሞከራችን በፊት ሥነ-መለኮት ያጠናን፥ ስለ ሚሲዮናዊነት ያጠናን፥ የሥነ ሰው እውቀት ያለን መሆን አለብን?
* ይህን የወንጌል ሥራ ያለ እነዚህ ድጋፍ ብቻውን ለመሥራት እየሞከርን አይደለምንም? የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የት ላይ ነው የሚመጣው? የእግዚአብሔር ቃል ኃይሉን አጥቷል ማለት ነው?

እነዚህ በእርግጥ አስቸኳይና መልስ የሚጠይቁ ትክክለኛ ጥያቄዎች ናቸው። እስቲ ባጭሩ የሚከተለውን እንይ፦

**እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራው የሚችለውን ነገር በጭራሽ ለመሥራት መሞከር የለብንም፤ በሌላ በኩል ደግሞ እኛ እንድንሠራው ያዘዘንን ነገር እግዚአብሔር እንዲሠራልን መጠበቅ የለብንም!**

መሥራት የሌለብን ምንድነው? ኃጢአተኝነታቸውን እንዲረዱ ማድረግ፥ እንዲለወጡ ማድረግ እንዲያውም «ወደ እውነት ሁሉ መምራት» በፍጹም እኛ ልንሠራቸው የምንችላቸው ነገሮች አይደሉም።

እኛ እንድንሠራው የሚጠበቅብን ምንድነው? የእግዚአብሔርን ቃልና በውጪ ላሉት ምሥጢር የሆነውን ወንጌል በግልጽ፥ በድፍረት፥ በጸጋ፥ በዕውቀትና በጥበብ

ይዘቱ በሚጠይቀውና በሚያስፈልገው መጠን ማስተላለፍና ማወጅ ይገባናል። (ይህ ጉዳይ በሚቀጥለው ምዕራፍ በደንብ ይብራራል።)

## ሰው የነባራዊውን ዓለም አመለካከት የሚወስነው ለመልእክታችን ባለው ግንዛቤ መሠረት ነው።

ይህንን ነገር እናውቀው ይሆናል፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን የምናነበው በራሳችን የነባራዊው ዓለም አመለካከት ‹መነፅር› መሆኑን መገንዘብ አለብን። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስን የምንተረጉመውና በሥራ ላይ የምናውለው እንደ አካባቢያችን ሁኔታና ባህላችን በሚመራን መንገድ ነው። በሌላ አካባቢና ባህል ውስጥ ያሉት ሰዎች ደግሞ ያንኑ በተለየ መልኩ ይገነዘቡታል። በእርግጥ ይህ ነገር መሠረታዊ የሆኑትን ነገሮች በፍጹም መንካት የለበትም፤ ነገር ግን ውጫዊ የሆኑትን፣ በቅርፅ ወይም በመልክ እና በኑሮ ዘይቤ አንፃር ብቻ መሆን አለባቸው።

እስቲ ከ ‹ዓለም› አንድ ምሳሌ ልጠቀም፤ በዚህች ዓለም ላይ ላለው የድህነት፣ የፍትሕ መጓደልና ፖለቲካዊ ጭቆና ምክንያቶች በግላችን ባለን አተናተን መሠረት መፍትሔ የሆነ ነገር ለማምጣት እንፈልጋለን። ለነዚህ ችግሮች አንደኛው ቡድን ፍትሐዊ ያልሆኑ መዋቅሮችን ያማርራል፤ በተጨማሪም ፍትሐዊ ያልሆነ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይተረጉማል፤ እንዲሁም ለምን ሰፊ ልዩነቶች እንዳሉ ይተነትናል። እንዲሁም ለዓለም ችግር ምክንያት የሆነው የምዕራባውያን ኢኮኖሪያዊና ፖለቲካዊ የሆነ ብዝበዛ ነው ይላል። ሌላው ቡድን ደግሞ ከልቡ ሲያብራራ የሕዝብ ብዛት ያለቅጥ መጨመር፣ የመንግሥት ባለስልጣናት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የአስተዳደር ዝቅጠት፣ ሰዎች ለምርታማነት መጨመር ያላቸው ቀዝቃዛ አመለካከት ምክንያቶች ናቸው ይላል።

በተመሳሳይ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስሳዊ የሆኑት ፅንሰ ሐሳቦችም በተለያየ ጊዜ በተለያየ የባህል ይዘቶች ውስጥ የተለያየ አተረጓጎም አግኝተዋል። ለምሳሌ፡- የክርስቲያኑን ኅብረት ኃጢአት እንደሚጎዳው እያንዳንዱ ኅብረተሰብ በተፈጥሮው ለግለሰቦችና ለኅብረተሰቡ አጥፊና ጎጂ ነው ብሎ የሚያምንበትና የሚፈራው ነገር አለው። አንዳንድ ክርስቲያኖች እንደ ኃጢአት የሚታዩትን ነገሮች በሰፊው እስከ መዘርዘር ይደርሳል። እንግዲህ እነዚህ ክርስቲያኖች ወደ ሌላ ኅብረተሰብ ቢሔዱ እዚያ ያሉት ክርስቲያኖች በሙሉ ከበስተጀርባቸው ባሉት በተለያዩ ሁኔታዎች መሠረት ወይ ለዘብተኞች ናቸው፤ ወይም ዓለማዊነት ያጠቃቸው ናቸው፤ ወይም ደግሞ በሕግ ብቻ የሚኖሩና የተለዩ ናቸው ብለው ይደመድማሉ።



እንግዲህ ይህንን ነገር በተለይም የተለያየ ባህል ላላቸው ወንጌልን ስንሰብክ (ወይም ስናስተምር) በደንብ ልናጤነው የሚገባ ጉዳይ ነው።

ውጫዊ የሆነውን መያዣውን፥ ቅርፁን ወይም የግንኙነት ዘዴውን የግድ መቀየር ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም ዛሬ ያሉትን ሰዎችና ያሉበትን ሁኔታ እንዲመጥን ተደርጎ መቅረብ አለበት፤ ነገር ግን ይዘቱንና መልእክቱን ለእኛ መለወጥ እንዳለበት መስሎ ቢታየንም እንኳ በፍጹም መቀየር የለብንም። ለሰሚዎቹ ሲቀርብላቸው መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ከሚያስተምረው ጋር የሚሄድ መሆን አለበት። በኋላ እንደምንመለከተው አንድ መስካሪ ዓላማው ማድረግ ያለበት ነገር አለ፤ ይህም የሚመሰክርለት ሰው ያለበት ሃይማኖት ልክ በሰውዬው አዕምሮ ሥር ሰዶ ያስቀመጠውን ነገር የሚመስል እና በሰውዬው የነባራዊው ዓለም አመለካከት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ነገር በአዕምሮው ለመቅረፅ መሆን አለበት።

## በትክክል መናገር

በእርግጥ ሁላችን ግድግዳ ከመገንባት ይልቅ ድልድይ መገንባት አለብን፤ ነገር ግን የውሸት ምልክቶችን አለማስተላለፋችንን፥ ለማግባባት ስንል ነገሮችን አለመሸቃቀጣችንንና በምንጠቀምባቸው ዘዴዎች፥ ምልክቶች፥ ቃላቶችና ሐሳቦች ምክንያት የመጽሐፍ ቅዱስ ይዘት ስውር ወይም የደበዘዘ ላለመሆኑ እርግጠኞች መሆን አለብን፤ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ ለገለጻ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ናቸው።

ነገሩን እንዳለ መውሰድ የእስልምናን ስሕተት መሸፋፈን ብቻ ሳይሆን፥ ከክርስትናው መልእክት ይዘት ጋር ሲወዳደር እስልምና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማማ ሃይማኖት መሆኑን የሚያሳየውን መለያውንና ልዩነቱን ማጥፋትም ጭምር ነው። የሚቀጥለውም ጉልህ ደረጃ ሃይማኖቶችን ማደባለቅ ይሆናል ማለት ነው።

## እውነትን በፍቅር መናገር

«በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን፥ እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፣ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም ዕውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን» (2 ቆሮ. 10፡3-5)።

ነገር ግን ይህ በፍቅርና ለጠፉት በማሰብ መደረግ አለበት። እስቲ ፍራንሲስ ሼፈር እንደገና ይህን ሲተነትነው ያለውን እንመልከት:-

> «ፍቅር ቀላል ነገር አይደለም፤ ስሜታዊ የሆነ ማስገደድም አይደለም፤ ነገር ግን አልፎ በመሄድና በሌላው ሰውዬ ቦታ በመቀመጥ ችግሩ ለሰውዬው እንዴት እንደሚታየው ለማየት መሞከር ነው። ፍቅር ለግለሰቡ እውነተኛ የኃላፊነት ስሜትን የሚያመጣ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያስታውሰን ‹እንደራሳችን› ሰውዬውን መውደድ አለብን። ይህ የምስክርነታችን የምንጀምርበት ሥፍራ ነው።»

ያለ መንፈሳዊና ቀና አመለካከት ወንጌልን መስበክ ትርጉም የለሽ የጭከና ተግባር ነው፤ ምክንያቱም ምናልባት የሚለወጠውን ሰው የሞት አደጋ፥ ወይም ሙሉ በሙሉ ተወግዞ መገለል እና ከሚወደው ቤተሰቡ መለየትን ሊያስከትል ስለሚችል ነው። ስሜታዊ ያልሆነና የክርስቶስ የሆነው ፍቅር (ለክርስቶስ እንኳ ባይሆን) እውነትን እንዴት እንደምንናገር ይመራናል፤ (ኤፌ. 4:15)።

---

| አድማጮችንን በደንብ የምንረዳው ከሆንና ስለ እርሱም በደንብ የምንቆረቆር ከሆን፥ አሉታዊ የሆነን ነገር በተናገርን ቁጥር ቢያንስ ቢያንስ እርሱን የሚጎዳውን ያህል እኛንም ይጎዳል። |
|---|

## ግንኙነትና ተግባሩን መረዳት

ግንኙነትን መረዳትና ባህልን መረዳት የአንድ ሣንቲም ሁለት ገፅታዎች እንደሆ እንመለከታለን።

አብዛኛዎቻችን ብቸኛውና አጥጋቢው የአኗኗር መንገድ የኛው እንደሆ እንድናምን ተደርገን አድገናል። የተወሰነ የቡድናችን ክፍል መሆናችን ደግሞ ያን በድጋሚ ያረጋግጥልናል። እንዲያውም እውነተኛና ትክክለኛ ለሆነው እምነታች ለመሞት እንኳ እናስብ ይሆናል።

ይህ ሃይማኖትን በተመለከተ ደግሞ እውነት ነው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አሁ እንኳ በአንድ ሃይማኖት ሥር ያሉ የተለያዩ የእምነት ክፍሎች እርስ በርሳቸ በጥርጣሬ ዓይን እንደሚተያዩት የተለያየ ሃይማኖት ያላቸው ደግሞ የበለ ያደርጉታል። ክርስቲያኖች እንጂ ለምን ሙስሊም፥ ወይም ፕሪስቢቴሪያን፥ ወይ የይሖዋ ምስክር፥ ወይም ሞርሞን፥ ወይም አዲሱ የሐዋርያት ቤተክርስቲያን አማ እንዳልሆንን በዝርዝር እንግለፅ ብንል ምናልባት ምክንያታችን አጥጋቢ ላይሆ



ይችላል። ሐሳባዊ ከሆነው ጭብጥ ተነሥተን እንቀጥል ይሆናል፤ ይህን ጭብጥ እኛ (ወይም ማንኛውም ሰው) እውነት ነው ብለውን ተቀብለነዋልና። አንድ ሰው እኛ የምናምንበትን ቢቃረን፥ ትተነው እንሄዳለን፤ ወይም እንከራከረዋለን። ከዚህ በኋላም ክርክሩን ብንሸነፍ እንኳ መጠነኛ ተጠራጣሪዎች ወይም ወግ አጥባቂዎች እንሆን እንደሆን እንጂ እዛው ባለንበት እንጸናለን። ብዙ ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስና በክርስቶስ ላይ ኃይለኛ የሆነ ተቃውሞና ነቀፌታ በሙስሊሞች ሲካሄድ ሰምተው ወይም አንብበው መልስ ስለሌላቸው ዝም ብለዋል። ነገር ግን ሙስሊም ለመሆን በፍጹም አያስቡም ለማለት ይቻላል። በተመሳሳይ መልኩ ሙስሊሞችም እንዲሁ ያደርጋሉ፤ እንዲያውም ከዚህ የባሱ ናቸው።

### ወንጌልን መስበክ ሊተላለፍ የማይቻለውን መልእክት ማስተላለፍ ነውን?

ይህ አባባል እንግዳ ሊመስል ይችላል፤ ነገር ግን እንድናደርግ የተጠየቅነው ዋናው ነገር ይኼ ነው። እስቲ እኔ መንፈሳዊ የአዕምሮ አስተሳሰብ ብዬ ልጠራው የወደድኩትን ነገር እንመልከት፤ በመሠረቱ ተቃራኒ አባባሎች ናቸው:-

> «እንዲሁ ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቁጠረን። እንደዚህም ሲሆን በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል» (1 ቆሮ. 4:1)።

ቃሉ በመጀመሪያ በተጻፈበት ቋንቋ ‹መጋቢ› የሚለውን ‹አይኮኖሞስ› ይለዋል። ኢኮኖሚ የሚለው ቃል ከዚህ የመጣ ነው። የክርስቶስ አገልጋይ ታማኝ (በግሪኩ:- ፒስቶስ) ቤት አያያዝ፥ ወይም ኢኮኖሚ የሚያውቅ መሆን ይጠበቅበታል። በምን? የእግዚአብሔርን ምሥጢር በመያዝ በኩል። የመጀመሪያው የግሪኩ መጽሐፍ ‹ሚዩስቴሪዩን› ይለዋል፤ ይህ ማለት በተገለጸለት ሰው ዘንድ ብቻ የሚታወቅ ማለት ነው።

ኤፌ 6:19 ስለ ወንጌል ምሥጢር ይናገራል። በስፋት ስንመለከተው የእግዚአብሔር ምሥጢር ማለት ነው። የክርስቶስ ምሥጢር ማለት ነው። የክርስቶስ ምሥጢርና ትክክለኛውን የወንጌል መረዳት የሚያገኙት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የገለጸላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው። ይህ ደግሞ የሚፈጸመው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው!

ይህን ስናነብ ደግሞ ነገሮቹ የበለጠ ውስብስብ ይሆናሉ:-

> «...የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዲያበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ» (2 ቆሮ. 4:4)።

በምድር ላይ ምን ዓይነት ተአምር እንድንሠራ ነው ከእኛ የሚጠበቀው? መንፈሳዊ ዓይነ ስውራን ለሆኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን መገለጥ (መንፈሳዊ) መረዳት (አዕምሮአዊ) እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። ይህ ደግሞ ምሥጢር ነው።

እንደገና በዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን እንመለከታለን:- እግዚአብሔር የሠራውን ወይም ሊሠራ የሚችለውን ወይም ወደፊት የሚሠራውን እና እኛ እንድንሠራው የሚጠብቅብን ነገሮች ናቸው። ጳውሎስ እንዲህ ይላል:-

«ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፤ ... መናገር እንደሚገባኝ ስለ እርሱ በግልጥ እናገር ዘንድ ለምኑ» (ኤፌ. 6፡19-20)።

በመጀመሪያ ደረጃ እንዴት እርሱ ምሥጢሩን ሊደርስበት ቻለ?

«የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ፤ ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው፥ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጧል» (ቆላ. 1፡26)።

ለጳውሎስ፥ ለዮሐንስ፥ ለማቴዎስ፥ ለማርቆስና ለሉቃስ ወዘተ... የተገለጠላቸው ነገር አዲስ ኪዳንን አስገኘ:- እርሱም ክርስቶስ ነው! ስለዚህ እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን በቃሉ ገልጿል። ይህ የእግዚአብሔር ድርሻ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም የቃሉን መገለጥም ሰጥቶናል:-

«አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል» (ዮሐ 14፡26)።

የክርስቶስ ደቀመዛሙርት ይህን ምሥጢር የማወጅ ሥራ ተሰጥቷቸዋል፤ (ኤፌ. 6፡19)፥ መገለጥ የሚገባቸውን ያህል በግልጽ እንዲናገሩ (ቆላ. 4፡4)፥ ማለትም:- በዕውቀት (ቆላ. 4፡6፤ 1ኛ ጴጥ 3፡15)፥ በጥበብ (ቆላ. 4፡5)፥ በጸጋ (ቁ. 6)፥ እንዲሁም በድፍረት (ኤፌ. 6፡20)። ይህን ለማድረግ እንድንችልና የታወረው የማያምኑት ሐሳብ እንዲከፈት ለማድረግ መጸለይ አለብን።

በዚህ ምዕራፍ ግንኙነት ብለን የምንጠራውን ጥቂት ጠለቅ ብለን ለማየት እንሞክራለን። እንደተመለከተነውም በአዕምሯዊና በመንፈሳዊ መሐል ሚዛን ለመጠበቅ እንሞክራልን።

## የግንኙነት ዘዴዎች

«ግንኙነት ማለት በአዕምሮዬ ያለውን አንድ ሐሳብ በከንፈሮቼ አሳልፌ ወደ ሌላው ሰው አዕምሮ ውስጥ ማድረስ ነው። በቂ የሆነ ግንኙነት የምንለው ለሌላው



ሰው አዕምሮ ልክ ከኔ በወጣበት ዓይነት በጥሩ ሁኔታ ሲደርስ ነው። እኔ ላስተላልፍ የምፈልገውን ነጥብ በበቂ ሁኔታ ለይቼ ማወቅ አለብኝ። የምንጠቀምባቸው ቃላት ለማስተላለፍ የምንፈልገውን ሐሳብ ለመተርጎም ብቻ የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች ናቸው ...»

(«በዚያ ያለው እግዚአብሔር» በፍራንሲስ ሼፈር)

ከአካላዊ ቋንቋ ሌላ አሳብን ለማስተላለፍ ምንም ሌላ መሣሪያ የለንም። ሐሳብን ለማስተላለፍ ቃላት ነው ያለን።

ቃላትን ሳንጠቀም በምልክት ቋንቋ በመጠቀም ልንገልጻቸው የምንችላቸው ድርጊቶች አሉ። ለምሳሌ:-

«እርቦኛል!»

«ራሴን አሞኛል!»

ነገር ግን እንዴት ነው በምልክት የምንናገረው?

«በጸጋው በእምነት ድነናል!»

የሚለውን እንዴት ልናወጣለት እንችላለን? ዓለማዊ የሆኑ ነገሮችን በምልክት ቋንቋ ለማስተላለፍ ቀላል ነው። በአዕምሮ ያለ ውስብስብ አሳብን ለማስተላለፍ ግን ከባድ ነው፤ ከዚህ ሌላ መንፈሳዊ የሆነውን መልእክት ለማስተላለፍ ደግሞ እጅግ በጣም ከባድ ነገር ነው። እስቲ ይህን ለመተንተን እንሞክር።

ቃላት ከተጠቃሚዎቻቸው ጋር ተዘምዶ አላቸው።

«እርቦኛል» ብዬ ብናገር ይህ አባባል ሶውጀት በተባለው የሳይቤሪያ የፖለቲካ እሥረኞች ማጎሪያ ውስጥ ላለ ሰውና የእራት ሰዓት ከመድረሱ ግማሽ ሰዓት በፊት የበረዶ ቤቱን ከፍቶ ለሚቃኝ የተለያየ ትርጉም ይኖረዋል። ይበርዳል ወይም ይሞቃል በምልበት ጊዜ በኤስኪሞ የሚኖረውና ማቀዝቀዣውን ሞምባሳ ውስጥ የሚኖረው ሰው በተለያየ ደረጃ ይረዱታል።

አንድ ቃል በጣም የተወሰነ መልእክት ያለውና ግልጽ በሆነ ቁጥር በይዘቱ ከሌላው ባህል ልዩ የሚያደርገው ነገር እየጨመረ ይሄዳል።

እስቲ ይህን ነገር በጥልቀት እንመልከት። በአሜሪካ በቤቴል ኮሌጅ ውስጥ የቋንቋ ምሁር የሆነው ዶናልድ ኤን ላርሰን ይህን አስተውሏታል።

«ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ሲገናኙ የሚተያዩት ንጹሕ በሆነ አመለካከት ሳይሆን፥ በየቡድናቸው በተፈጠረው ሁኔታና በዚያ ነጥብ ላይ እያንዳንዳቸው በሚያውቁት አንፃር፥ እንዲሁም በአዕምሯቸው በተቀረፁት መሠረት ነው።

አንዱ ሌላውን እንደ ባዕድ ይመለከታል። ‹የሆነ የአስተሳሰብ ግድግዳ› በመሐከላቸው ስላለ የተለያዩ ናቸው። ምናልባት ስለ ዕለቱ የአየር ሁኔታ በነፃነት ሊያወሩ ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን ዋና የሆነውን የሕይወት ጉዳይ ለምሳሌ:- ስለ ነባራዊው ዓለም ስላላቸው አመለካከት፥ ስለ ኑሮ ዘይቤ፥ ወዘተ እርስ በርስ ሊጣጣሙ አይችሉም። በዚህ ጊዜ ግጭት በመሐላቸው ይፈጠራል።

ሁሉም ሰው ከማያውቀው ነገር ጋር ፊት ለፊት በሚጋፈጥበት ጊዜ ከዚህ በፊት ከሚያውቀው ነገር ጋር በሚያደርገው ማወዳደር ላይ ይወሰናል። እንደተለመደው የሚያወቀው ነገር ባሕርያት ወደማይታወቀው ነገር ይተላለፋሉ። እስቲ ይህን ለማብራራት እንሞክር፤ የመጀመሪያዎቹ መኪናዎች ለሕዝብ በታዩ ጊዜ ሰው ሁሉ ከመኪናዎቹ ፊት የሚጎትቷቸውን ፈረሶች ወይም በሬዎች ለማየት ይፈልግ ነበር። የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ሁልጊዜ ከሚጎተቱ እንስሶች ጋር የተያያዙ ነበርና። ልክ እንደዚሁ አንድ ክርስቲያን፡ ሙስሊሞች አንድ አምላክ ነው የሚያምኑት ተብሎ ሲነገረው፥ ይህ አምላክ በእርግጥ እግዚአብሔር ነው ብሎ ባሕርዩን ሁሉ አንድ አድርጎ መመልከቱ የተለመደ ነው። ነገር ግን ጥያቄው በአንድ አምላክ እናምናለን? ሳይሆን ይህ አምላክ ራሱን የገለጸው እንዴት ነው? ምን ይመስላል? የሚለይበት ስሙ ምንድነው? መሆን አለበት። ጠንቃቃ የሆነ ተማሪ የአንድን ነገር ላዕላይ የሆነ መመሳሰልን አይደለም የሚመለከተው ነገር ግን መሠረታዊ የሆነውን ልዩነት በደንብ ያስተውላል። በተጨማሪም የእግዚአብሔር የሆኑትን ባሕርያትና ከዚህም የሚመጡትን ውጤቶች ሁሉ ይመለከታል።

ለርሰን በመቀጠል እንዲህ ብሏል:- «አንድ ክርስቲያን፥ ሙስሊሙ ከሚያውቀው ነገር የተወሰነውን ማወቅ አለበት፤ ምክንያቱም በራሱ ልምምድና እውቀት መሠረት ለመጠቀም የሚቻለው የዚያን ጊዜ ነው»።

«የክርስቲያን ንግግሮች በሙስሊሙ ጆሮ ውስጥ ሲገቡ የንግግሮቹ ትርጉም የሚቀነባበረው አስቀድሞ በሙስሊሙ አእምሮ ውስጥ ባለው መሠረት ነው። ልክ እንደዚሁ የሙስሊም ንግግሮች በክርስቲያኑ ጆሮ ሲገቡ፥ ትርጉማቸው አስቀድሞ በክርስቲያኑ አእምሮ ባለው ነገር መሠረት ይወሰናል»።

«ለየት ባለ መልኩ ስናስቀምጠው:- አንድ ክርስቲያን የሚያውቀውን ሲያስተላልፍ ሙስሊሙ ካዳመጠ በኋላ፥ ከሚያውቀው ነገር ጋር ያወዳድረዋል፤ በዚያው መሠረት ትንታኔ ይሰጠዋል። በተመሳሳይ መልኩ ሙስሊሙ የሚያውቀውን ሲያስተላልፍ፥ ክርስቲያኑ አስቀድሞ በአእምሮው ባለው ነገር መሠረት ይተነትነዋል። ይህ ማለት ክርስቲያኑ የላከውን መልእክት ሙስሊሙ በሚያውቀው መሠረት ነው የሚያደራጀው፥ ክርስቲያኑም ይህንኑ



ነው የሚያደርገው። እያንዳንዱ የሚያስተላልፈውን ነገር ይቆጣጠራል። ነገር ግን በተላለፈው መልእክት ላይ የተቀባዩን መረዳት ለመቆጣጠር ያዳግታል። ከዚህም ባሻገር በአንድ አእምሮ ውስጥ ያለውን ነገር ማስወገድ አይቻልም። በዚህ አንፃር አንድ ሰው ሊያደርግ የሚችለው የመጨረሻ ነገር ነገሩን ሊያስተካክሉ ወይም ሊያቀናጁ የሚችሉ ነገሮችን መናገር ብቻ ነው።

«ሙስሊሙ የክርስቲያኑን እውነተኛ ነገር ሊረዳና ሊቀበል የሚችለው፥ ክርስቲያኑ የሙስሊሙን እውነተኛ ነገር ሲረዳለትና ሲያደንቅለት ብቻ ነው።»

«ስለዚህ ክርስቲያኑ የሙስሊሙን ልብ ለመንካትና በአጥጋቢ ሁኔታ ጥሩ ነጥብ ላይ ለመድረስ ከፈለገ፥ ለመናገር የተዘጋጀ መሆን አለበት፥ በተጨማሪም ለመስማትም የተዘጋጀ መሆን አለበት።»

«አጠቃላይ የሆነው ችግር ተቀናንሶ ዓይነተኛ ወደሆነው የመወዳጀት ችግር ላይ ይደርሳል። ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የተለያየ «የዘር» ጎራ አላቸው። በያሉበት ቡድን ውስጥ እያንዳንዳቸው የተለያየ ነገር ያውቃሉ፤ የተለያየ የቋንቋ ክልል አላቸው፤ ከሌሎች ጋር የሚገናኙት በተለያየ ሁኔታ ነው፤ እንዲሁም የተለያየ እምነት ነው ያላቸው።»

በፋለር ሴሚናር ውስጥ የሥነ-ሰው (አንትሮፖሎጂ) ፕሮፌሰር የሆነው ፖል ሐይበርት በዚህ ላይ እንዲህ ሲል አክሎበታል:-

«ክርስትናን አዲስ ባህል ወዳላቸው ሰዎች ስናስገባ በአዲሱ ባህል ቋንቋ መተርጎም ብቻ ሳይሆን የእነሱን ባህል የሐሳብ ቅርፅ፥ ምልክቶችና ልምምዶች የያዘ መሆን አለበት።»

ሙስሊሞች፥ ክርስቲያኖች፥ ሂንዱዎች ሌሎችም የተወሣሠበ የአስተሳሰብ መዋቅር አላቸው። ቃላት በሃይማኖቱ፥ በባህሉና በማኅበራዊ ጉዳዮቹ መሠረት ላይ የተቀረፁ ናቸው፤ ይህ ግን ምናልባት በሌሎቹም ቋንቋዎች አንድ ዓይነት ሊሆን ይችላል። እንግዲህ እንደተባለው ለስኬታማ ግንኙነት በተቀባዩ ዘንድ አስቀድመው የሚታሰቡ ነገሮችን ማስወገድና ማስተላለፍ የምንፈልገውን ነገር ማስገባትን መማር አለብን። የዚያን ጊዜ ነው መልእክታችን በተቀባዩ ዘንድ መረዳትን የሚያገኘው። መጽሐፍ ቅድስ ይህን እንዲህ ብሎ ያስቀምጠዋል:-

«ከምታነቡትና ከምታስተውሉት በቀር ሌላ አንጽፍላችሁምና፤ ... በከፊል ስለ እኛ እንዳስተዋላችሁ ፈጽማችሁ ታስተውሉት ዘንድ ተስፋ አደርጋለሁ» (2 ቆሮ. 1፡13-14)።

«ነገር ግን የሚያሳፍረውን ሥውር ነገር ጥለናል። በተንኮል አንመላለስም የእግዚአብሔርንም ቃል በውሸት አንቀላቅልም፡ እውነትን በመግለጥ ግን በእግዚአብሔር ፊት ለሰው ኅሊና ሁሉ ራሳችንን እናመሰግናለን» (2 ቆሮ. 4፡2)።

ይህ በሌላ ቃል ተረጋግጧል፡-

«...የእግዚአብሔርንም ጸጋ በእውነት ከሰማችሁበትና ካወቃችሁበት ቀን ጀምሮ በእናንተ ደግሞ እንዳለ እንዲሁ በዓለም ፍሬ ያፈራል ያድግማል» (ቆላ. 1፡6)።

እስቲ ይህንን እንርሳው፡-

## አንድ ሙስሊም ወንጌልን የሚረዳው እኛ እርሱንና ሃይማኖቱን በምንረዳበት መጠን ነው

በእርግጥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ዘወትር እንደሚያደርገው በትክክለኛው መንገድ በዚህ መሐል ገብቶ የሰውዬውን አእምሮ ሊከፍተው ይችላል። ነገር ግን በመሠረቱ መንፈሳዊ እድገትና መለወጥ የሚመጣው ሰውዬው እውነት የሆነውን ነገር አውቆና ተቀብሎት በፈቃደኝነት ሲገዛለት ነው። ይህ ግንዛቤ ሊመጣ የሚችለው መንፈሳዊ የሆነውን ይዘት በመረዳት ነው። ይህንን የማስተላለፍ ሂደት ደግሞ ለሙስሊሙ በጥበብና በማስተዋል በመናገራችን ላይ ይወሰናል። ይህንን ማድረግ የምንችለው ደግሞ ሰውዬውንና ሃይማኖታዊ የሆነውን ይዘቱን በትክክል ስንረዳ ብቻ ነው።

ይህ ጉዳይ የሚያጠቃልለው የሙስሊም ጓደኞችን ግላዊ ይዘቱን ወይም ባሕሪዩን ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ የእምነቱ ይዘትም ምን እንደሆነ መረዳትም ጭምር ነው። በተጨማሪም እምነቱ ለእርሱ የሚሰጠውን ትርጉም፥ ለክርስትና መልእክት ያለው ተቃውሞ ምን እንደሆነ መረዳትም ጭምር ነው። በተጨማሪም እምነቱ ለእርሱ የሚሰጠውን ትርጉም፥ ለክርስትናው መልእክት ያለው ተቃውሞ ምን እንደሆነ እንዲሁም ምን አይነት ይዘት ያለው ሃይማኖታዊ ቃላት ለእርሱ ትርጉም እንደሚሰጡት ማወቅ አለብን።

እንዲህ ዓይነት ውስጣዊ የሆነ እውቀት እንዴት ማግኘት እንችላለን? ክርስቲያኖች ስለ እስልምና ከጻፉቸው መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም በመርህ ደረጃ የምንቀበለው አለ። በሐሳብ ደረጃ አንድ ሰው በደንብ ከሠለጠነ ሙስሊም ጋር ግላዊ የሆነ መቀራረብ ይፈጥራል። ከዚያ በኋላ በሚኖረው ንግግር ማወቅና መገንዘብ የሚፈልገውን በጥልቀት ለማግኘት ይቻላል። ይህ ጊዜን ይጠይቃል፤ በተጨማሪም



ቁልፍ ቃል የሆነውን (ማዳመጥን) ይፈልጋል። ሙስሊማዊ የሆኑ መጻሕፍት ምናልባት ለዚህ ምትክ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ግን የተለያዩ መጻሕፍት ማግኘት አለብን። በእርግጥ መጻሕፍትን ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም። መጽሐፍ መልእክትን ማስተላለፍ ብቻ እንጂ፤ ከዚህ ሌላ የሚሠራው የለም።

ለዚህ ምን ያህል ጊዜ መታገሥ አለብን? በአጥጋቢ ሁኔታ ተቀባይነት ያለው ግንኙነት መፍጠር እንድንችል ምን ያህል የእውቀት ደረጃና መረዳት ሊኖረን ይገባል?

በግልጽ እንደሚታወቀው አብዛኞቹ ለሙስሊሞች የሚመሰክሩ ክርስቲያኖች ለዚህ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ችሎታ ያላቸው ወይም ዝግጁ የሆኑ ይመስላቸዋል። እንዲህ ባይሆን ኖሮ ለሙስሊሞች መመስከሩን አይሞክሩትም ነበር። እንዳጋጣሚ ወይም እንደ ዕድል ሆኖ የብቃት ሰርተፊኬት የሚሰጥ ምንም አካል የለም። ምንም እንኳ አንድን ወይም ሌላን የተሰጠ ምስክርነት ተስፋ የማስቆረጥ አደጋ ቢኖረውም፥ (ይህ ግን ከእኔ ይራቅ) - አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ፤ በጣም ብዙ ቅናት ያላቸው ነገር ግን በትክክል ያልተዘጋጁ ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች ለመመስከር ይሞክራሉ። ይህ ነገር በሙስሊሞቹ የሚያመጣው ዓለመረዳትን ወይም በተሳሳተ መንገድ መረዳትን ብቻ ሳይሆን፥ ክርስቲያኖች ተጠያቂ (ሎጂካል) ያልሆነና የተበላሸ ሃይማኖት ነው የሚከተሉት ለሚለው አስተሳሰባቸው አዎንታዊ አስተዋፅኦ ያስገኝላቸዋል። የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተዋል፤ ስለሆነም ቃሉ በጊዜው የራሱን ይሠራል፥ እያልን ራሳችንን በቀላሉ በማጽናናት መቀጠል ያለብን አይመስለኝም። ይህ እውነት ሊሆን ቢችልም፥ መርአችን ግን፡-

## ለውጥ የሚያመጣው እኔ የምናገረው ሳይሆን ሰሚው የሚረዳው ነገር ነው።

እስቲ በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ከዶ/ር ፍራንሲስ ሼፈር የተጠቀሰውን እንደገና እንመልከት፡-

«ግንኙነት ማለት በአእምሮዬ ያለውን አንድ ሐሳብ በከንፈሮቼ አሳልፌ ወደ ሌላው ሰው አእምሮ ውስጥ ማድረስ ነው። በቂ የሆነ ግንኙነት የምንለው ለሌላው ሰው አእምሮ ልክ ከኔ በወጣበት ዓይነት በጥሩ ሁኔታ ሲደርስ ነው።» እንግዲህ መለየት ያለብን የሚከተሉትን ሁለት ነገሮችን ነው፡-

### ተጨባጭና ሐሳባዊ ግንኙነት

ለእኛ እውነት የሆነ ነገር ለሌሎች እውነት ላይሆን ይችላል። አበበ በጣም ለሚወዳት የአልማዝ ያለው ስሜት ለእርሱ እውነት ነው። የሊዛ እናትም ደግሞ እሷን

ይወዷታል፤ ነገር ግን አንድ ዓይነት እውነታ አይደለም። ጓደኞችም ‹ይወዷታል›፤ ነገር ግን የአበበ ፍቅር የተለየ ነው። በእርግጥ የእርሷ ባልደረቦችም ሌሎች ሴቶችን ሊያፈቅሩ ይችላሉ። በፍቅር መጠመድ ምን እንደሆነ እውነተኛ ልምምድ አላቸው። ነገር ግን አበበ ከአልማዝ ጋር መዋደድ ምን እንደሚመስል ብቻ ነው የሚያውቀው። ይህ ለእርሱ የተለየ ልምምድና እውነት ነው።

በተመሳሳይ መልኩ ተጨባጭና ሐሳባዊ የሆኑ መንፈሳዊ ልምምዶች አሉ። ሁለቱም ወደ እኛ ሲመጡ እውነት ናቸው። ይህ ልምምድ ግላዊ እየሆነ በሄደ ቁጥር የበለጠ የከበረ ይሆናል፤ ግን ሐሳባዊ ሊሆን ይችላል። ምናልባት እኛ በጣም የምንወደውና የምናከብረው ልምምድ ይሆናል፤ ነገር ግን ለሌላው ሰው ተመሳሳይ የሆነ መልእክት ላይኖረው ይችላል፤ ወይም ጭራሽ በተሳሳተ መንገድ ተረድቶትና ሰውዬው በሌላ ደረጃ ከተለማመደው ጋር አወዳድሮት ነገሩ ላይገባው ይችላል። «እግዚአብሔር ጸሎቴን በአስደናቂ መንገድ መለሰልኝ!» የሚለው ዓረፍተ ነገር በሰሚው የመረዳት ደረጃ ምላሽ ሲያገኝ፡- «አ! እኔ ዘወትር እንዲሁ ዓይነት ልምምድ ነው ያለኝ!» የሚል ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ ሙስሊሙ ፍጹም የተለየውን የራሱን ሁኔታ በአእምሮው አኑሮ ተመሳሳይ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል። ወይም ምናልባት ክርስቲያኖች በቀን በቀን መለኮታዊ የሆነ ነገር ያያሉ፤ ይህ ደሞ ሁሉም ሰው የሚያየው ነው በማለት ሊደመድም ይችላል።

እስካሁን እንግዲህ ሐሳባዊ ስለሆነው ልምምድ እያሰብን ነው። ይህንን የሕይወት ምስክርነት መስጠት ብለን እንጠራዋለን።

ተጨማጭ የሆነ ግንኙነት ማለት የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ማስተላለፍ ማለት ነው። «እግዚአብሔር...ብሏል» ማለቱ ምናልባት በእምነት ላይ የተመሠረት ስለሆነ ሐሳባዊ ነው ሊባል ይችል ይሆናል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደሆነ ሊታወቅ ይችላል፤ በእርግጥም እንዲሁ መሆን አለበት! ታማኝና በተጨባጭ ነገሮች የሚያምን ሰው የወንጌልን እውነቶች ሲሰማና የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኛነት የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን ሲያገኝ፥ ስሜታዊና አእምሮአዊ በሆነ መንገድ ወደ መስማማት ከመምጣቱ በፊት ምናልባት ጊዜ ይወስድበት ይሆናል። ነገር ግን ከዚህ በኋላ ወደ ስምምነት ይመጣል። ማንኛውም ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛነት መፈተን ይችላል። ይህ ደግሞ ማንም ወደደም ጠላም ማስረጃ ያለው እውነት ስለሆነ ተጨባጭ ያደርገዋል።

ስለዚህም ወንጌልን መመስከር በዘፈቀደ ወይም እንደቀላል ነገር በፍጹም መወሰድ የለበትም፤ ነገር ግን ሐዋርያት እንዳደረጉት ተጨባጭ በሆነ መንገድና በእውነት ላይ ተመሥርቶ እንዲቀርብ በደንብ መቀመር አለበት።



ይህ አባባል የሕይወት ምስክርነት በመስጠት ሰዎች ወንጌልን ከማካፈል እንዲያፈገፍጉ ለማድረግ የታሰበ አይደለም። ነገር ግን በመርሕ ደረጃ ይህ ተጨባጭ ለሆነው ወንጌል ድጋፍ ሰጪ ሆኖ መቅረብ አለበት።

**ወንጌልን የማስተላለፍ ግንኙነት ሊገባ የሚችል፥ ማስፍረጃ ያለው፥ ትርጉም ያለው (ለአድማጩ!) እንዲሁም የሚመስጥ መሆን አለበት።**

### 1. የወንጌሉ እውነቶች

ይህ ነገር ለብዙ ክርስቲያኖች ግልጽ እንዳልሆነ አምናለሁ። ወንጌል እጅግ ብዙ ይዘት ስላለው ተቀባዩ አስቀድሞ የተወሰነ እውቀት ከሌለው በስተቀር በአንድ ምሽት ወይም በሁለት ምሽት ሁሉንም ለማስረዳት የማይቻል ነው። እኛ፥ ዋዛ በሌለው፥ ሥልጡንና «ጥቃቅኑን» ለማወቅ እምብዛም በማይጕጓ ኅብረተሰብ ውስጥ ስለምንመላለስ፥ አንድ ወጥ የሆነውን ቀልጣፋ ውጤት የሚያስገኘውን አቅርቦት የመጠቀም ልምምድ አለን። በሙስሊሞች፥ በሂንዱዎች ወይም በቡድሃዎች ዘንድ ግን ይህ የሚሠራ አይደለም፤ ምክንያቱም ልናስተላልፈው የምንፈልገውን መልእክት በዝርዝር ስለማይረዱት ነው። ግልጽ ያልሆነ የግንኙነት ጭላንጭል ቢኖርም እንኳ ተቀባዩ መልእክቱን በደንብ ስለማይረዳው ጭምትና ጠበቅ ያለ ውሳኔን ለማድረግ ይቸገራል።

ከሁሉ በፊት የያንዳንዳችን ፈጣሪ የሆነውና ሕይወታችንን በእጁ የያዘው ዘላለማዊ፥ ሁሉን ቻይ፥ ሁሉን ዐዋቂው፥ በሁሉም ስፍራ የሚገኘው፥ ጻድቁ እግዚአብሔር አለ። የመንፈሳዊ ንግግሮች ሁሉ መጀመሪያ ላይ እግዚአብሔርን ማቅረብ አለብን። ስብዕና የሌለው፥ በሩቅ ያለ መለኮታዊ ኃይል አድርገን ሳይሆን፥ ስብዕና ያለው አፍቃሪ እግዚአብሔር፥

ከእግዚአብሔር አንፃር የምንመለከተው ሰውን ነው። እንደ ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ሰውም የተፈጠረው በእግዚአብሔር ነው። የተፈጠረውም የእግዚአብሔር የፍቅሩ መግለጫ እንዲሆንና ከጌታም ጋር ኅብረት እንዲያደርግ ነው። ከዚህ የተነሣ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮ በሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ላይ የበላይ እንዲሆንና በየዕለቱ ከሚያጋጥሙት የሕይወት ጉዳዮችና ጊዜያዊ ከሆነው ሥጋዊ ነገር ባሻገር እንዲወስን ፈቃድ ተሰጥቶታል። ነገር ግን ሰው የእግዚአብሔርን ቅዱሱን ፈቃድ እያወቀ፥ በፈቃደኝነት ሁልጊዜ በመጣስ ላይ ይገኛል። የመጀመሪያው ኃጢአት «የሰውን ውድቀት» አመጣ። ከዚህ በኋላ በሰው ላይ ቋሚ የሆነ ኃጢአትን እንዲሠራ የሚገፋፋው ባሕርይ መጣ። ይህ ደግሞ እግዚአብሔርንና ሰውን ያለያየ ነገር ነው። ሲ.ኤስ.ሊዊስ «የሥቃይ ችግር» በተባለው ግሩም መጽሐፉ እንዲህ ብሏል፡-

« . . . ኃጢአትን በማኅበራዊ ሥነ-ምግባር አንፃር ሳይሆን በበለጠ ጥልቀት ባለውና ጊዜ በማይወስነው ደረጃ መመልከት አለብን።»

«ይህ ኃጢአት በቅዱስ አውግስጢኖስ አገላለጽ መሠረት በትዕቢት ምክንያት አንድ ፍጡር (ማለትም:- የመኖር ህልውናው በራስ ሳይሆን በሌላው ላይ ፍጹም ጥገኛ የሆነ ፍጡር) ለራሱ ለመኖርና በራሱ ለመቆም የሚያደርገው እንቅስቃሴ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ኃጢአት ምንም ዓይነት የተወሳሰበ ማኅበራዊ ሁኔታ፣ ምንም ዓይነት ልዩ ልምምድ፥ ምንም ዓይነት ከፍተኛ የእውቀት ደረጃ የሚጠይቅ አይደለም። አንድ ፍጡር እግዚአብሔርን እንደ እግዝኢአብሔር፣ ራሱንም እንደ ራሱ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በጣም አስቸጋሪ የሆነው እግዚአብሔርን ወይም ራሱን እንደማዕከል አድርጎ የመምረጡ በር ይከፍትለታል።»

«ከእግዚአብሔር እንድንርቅ የሚስበን ነገር፥ ‹ወደ ቤታችን ማለትም ወደ ለመድነው እኔነታችን የመጓዙ ነገር›፥ የውድቀት ውጤት መሆኑን የግድ ማሰብ ያስፈልገናል።»

«ይህ በፍጡር በኩል የሚደረግ ራስን የመምረጥ ድርጊት የፍጡርንትን እውነተኛ ባሕሪይ በፍጹም ውሸት የሚሸፍነው ኃጢአት ነው። ስለ ኃጢአት አስቸጋሪ የሆነ አመለካከት፥ እጅግ በጣም ዘግናኝ መሆን አለበት፣ ወይም የሚያስከትለው መዘዝ በጣም የከፋ አይደለም የሚለው ነው።»

የኃጢአት ምንነት በሕግ ይወሰናል። በብሪታንያ በመንገዱ በስተግራ በኩል መንዳት ትክክል ሆኖ ሳለ፥ በፈረንሣይ ግን ወንጀል ነው። በዚያ ሕጉ፣ ተሽከርካሪዎች በመንገዱ በስተቀኝ መሄድ አለባቸው ይላል።

«ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤» በሮሜ 7:7 ይህን እናነባለን። ሰውን ለመምከርና ለመምራት እግዚአብሔር ሕግን ሰጠ። ነገር ግን ሰው እኛንም ጨምሮ ባለማቋረጥ ሕግን ተላልፎአል። የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድም የሚያሳዝን ነው:-

«እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈፅሞ ክፉ እንደሆነ አየ» (ዘፍ. 6:5)።

ምናልባት ከዚህ አባባል ጋር መስማማት ያስቸግር ይሆናል። አባባሉ የተጋነነ ሐሳብ አይመስልም እንዴ? ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን ሲያየው ይህን ይመስላል።



ኃጢአት የምንለው፥ ሰው ከእግዚአብሔር ጥገኝነት ነፃ ወጥቻለሁ ብሎ ነፃነቱን ሲያውጅ፣ እንዲሁም ያለ እግዚአብሔር ዛሬም ሆነ ለዘላለም መኖር እችላለሁ ሲል ነው። አለማመን ኃጢአት ነው፤ (ሮሜ 14:23)። የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፍ ኃጢአት ነው (1 ዮሐ 4:3)፤ በእርግጥ ሁሉም አመፅ ኃጢአት ነው፤ (1 ዮሐ. 5:17)፤ በተጨማሪም እንዲሁ በቀላሉ የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም፤ (ሮሜ. 1:20፤ 2:1፤ ዮሐ. 15:22)። (ነገር ግን ይቅርታ የሌለው አይደለም!)

«እነርሱ ባለማወቃቸውና በልባቸው ደንዳናነት ምክንያት ልቡናቸው ጨለመ፤ ከእግዚአብሔርም ሕይወት ራቁ፤ ደንዝዘውም በመመኘት ርኩሰትን ሁሉ ለማድረግ ራሳቸውን ወደ ሴሰኝነት አሳልፈው ሰጡ» (ኤፌ. 4:18-19)።

በማለት የእግዚአብሔር ቃል ሲያጠቃልል፥ በእርግጥ በብሉይ ኪዳን ኃጢአታቸው ነገሮችን ይወስን እንደነበረው ዛሬም እየተወሰነ መሆኑን ይገልጻል:-

«እነሆ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፤ ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም፤ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፤ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከናንተ ሰውሮታል» (ኢሳ. 59:1-2)።

በኃጢአት ምክንያት የመጣው ሙታንነት ሰው የእግዚአብሔርን ቦታ እንዳይመለከትና እንዳይረዳ ጋርዶታል። ይህ ኃጢአት አንድን ወይም ሌላን ሕግ መተላለፍ አይደለም፤ ወይም ሙስሊሞች ኃጢአትን እንደሚመለከቱት ትክክለኛ ነገርን አለማድረግ ማለት አይደለም። ነገር ግን ሰው ሙሉ በሙሉ በመንፈስ የሞተ ሆኖ ሳለ ትርጉም የለሽ በሆነ ትዕቢቱ ካለበት ምስቅልቅል ሁኔታ ራሱን ማውጣትና በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ማግኘት እንደሚችል፥ እንዲሁም ለኃጢአቱ ካሣ በመክፈል ራሱን ማዳን እንደሚችል ማሰቡ ነው።

ይህ ለእግዚአብሔር ቅድስና ዕውር መሆን፥ ሰው እግዚአብሔርን እንዳይፈልግ፣ እንዳያይ እንዲሁም የተሰጠውን የመታረቅ ዕድል እንዳይቀበል ያግደዋል፤ ምክንያቱም ሁሉም ሞኝነት ይመስለዋል። እግዚአብሔር ደግሞ እንዲህ ዓይነቱን መንፈሳዊ ትዕቢትና ዓመፅ በቸልታ አያልፈውም።

ከመጀመሪያ ጀምሮ እግዚአብሔር በደም መሥዋዕት አማካይነት ስርየትንና የመታረቅን ዕድል ሰጥቷል። እግዚአብሔር ለኃጢአታቸው መሥዋዕትን እንደከፈለ የሚያምኑ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምተዋል። በከፍተኛው ደረጃ ስንመለከት የሰዎችን ኃጢአት ሁሉ ተሸክሞ መሥዋዕት መክፈል የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ዮሐ. 1:29)። ነገር ግን ይህን የእግዚአብሔር ስጦታ እያንዳንዱ ሰው በግሉ ሊቀበለው ያስፈልጋል። ሌላ ምንም መንገድ የለም (ሐዋ. 4:12)። ይህ ደግሞ